# ፍካሬ

በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ(ኢሕአፓ)

ታትሞ የሚወጣ ሩባዊ

## ጥናታዊ የትንተና መፅሄት

ቅጽ 17 ቁጥር 1 የካቲት 2002 ዓ.ም.

## ስለ ፍካሬ ልታውቋቸው የሚገቡ ጉዳዮች

1. በፍካሬ የሚወጡ ጽሁፎች ሁሉ የፓርቲ አባላት የጻፏቸው ወይም የፓርቲው አቋሞች አይደሉም። የፓርቲውን አቋም የሚመለከት ጽሁፍ ሲወጣ ፓርቲው ይህንን ያስታውቃል።

2. የሚላኩ ጽሁፎች በአማርኛ የተዘጋጁ ቢሆኑ ይመረጣል።

3. የአመት ደንበኞች ለመሆን የሚሹ ሁሉ አመታዊ ክፍያው ለአራት አመት እትሞች 20 የአሜሪካን ብር ነው። ይህንኑ በፖስታ ሳጥን ቁጥራችን መላክ ይቻላል። የሚከፈለው በቼክ ወይንም በመኒ ኦርደር ለኢሕአፓ ነው።

4. ፍካሬ በአመት አራት ጊዜ ትወጣለች።

5. ጽሁፎች መላክ የሚፈልጉ በሀገራዊና አለም አቀፋዊ የፖለቲካ፤ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ጉዳዮች፣ ሥነ ጽሁፎችና ፓርቲ ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ ሊልኩልን ይቻላል። በተቻለ መጠን ጽሀፊዎቹ ስማቸውን አለበለዚያም የብዕር ስማቸውን ሊነግሩን ይገባል። የብዕር ሥም የሚጠቀሙ ከሕጋዊ እርምጃዎች አንጻር አግባብ ስላለው ለአዘጋጆቹ ብቻ ስማቸውንና አድራሻቸውን መግለጽ አለባቸው።

6. ጽሁፎቹ እስከተቻለ ድርስ በጣም ባይረዝሙ (ከ5-7 ገጽ) ባይበልጡ ይመረጣል። ለጥራትና ለመጠን ሲባል ጽሁፎች እርማት ሊደረግባቸው ይችላል።

7. የሚደርሱንን ደብዳቤዎች በየጊዜው እናወጣለን። ደብዳቤ የሚጽፉ ስማቸውንና አድራሻቸውን ከነስልክ ቁጥራቸው በትክክል እንዲያሰፍሩ እንጠይቃለን።

8. ርዕሰ አንቀጾቹ ከዝግጅት ክፍል የሚቀርቡ ናቸው።

| | |
|---|---|
| ዋና አዘጋጅ | ዶ/ር ዘነበ ተሾመ |
| ምክትል አዘጋጅ | ሃይሉ ወንዴ |

መጽሄቷን ለሚመለከቱ ግንኙነቶች በሚቀጥለው አድራሻ ይጠቀሙ።
FIKARE
P.O.BOX 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A

# ፍ ካ ሬ

በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ

ታትሞ የሚወጣ

ሩብ አመታዊ መጽሄት

ማውጫ


ገፅ

1. ርዕሰ አንቀጽ................................................................. 01

2. በ 2009 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ችግሮችና መፍትሄ ተብለው የተወሰዱ እርምጃዎች፣ ያስገኙት ጥቅምና ያስከተሉት ጉዳቶች።
ከኃይሉ ወንዴ................................................................. 02

3. ለሀገር ሻጭ ዘረኛ ቡድን ምንም ምህረት ሊታሰብ አይችልም።
ከፍኖተ ዴሞክራሲ የተገኘ................................................ 16

4. ኢሕአፓና የኢትዮጵያ የመከላከያ ፖሊሲ
የትዝብት አድማስ ቁ. 84
ጥር 16 ቀን 2002 ዓ.ም................................................ 19

5. ኢሕአፓና የኤኮኖሚ ፖሊሲ
የትዝብት አድማስ ቁ. 85
ጥር 26 ቀን 2002 ዓ.ም................................................ 22

6. የወያኔ የጅምላ አባላት ምልመላ የመጨረሻው የሀገር ማጥፋት ተልዕኮው ማስፈፀሚያ መሆኑን ማጤን ይገባል።
ከአ ዕምሮ በለጠ አዲስ አበባ........................................ 25

7. ከፍኖተ ዴሞክራሲ የዝግጅት ክፍል የተገኘ
ሀ. የካቲት 11 -- የተረገመ የርጉሞች ቀን...................... 28
ለ. ምን ማድረግ አለብን?............................................ 29

8. ከኢፖእአኮ የተገኙ
ጥቅሶች........................................................................ 32
ግልፅ ደብዳቤ
ሀ. ለደ/አፍሪካ ለፕሬዚደንት ያቀብ ዙማ የተላከ.................. 33
ለ. ለኖርዌይ መንግሥት ባለሥልጣናት የተላከ ..................... 34

9. Africom. A Recolonization Force?
By Lemma Tedla...................................................... 38

## ርዕሰ አንቀጽ

ፍካሬ የዚህን አመት የመጀመሪያ ዕትም የሀገራችንን የፖለቲካ፡ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ሁናቴ የሚተነትኑ የተለያዩ መጣጥፎችን አካተን ለንባብ አቅርበናታል።

በ 2009 ዓ.ም በኢትዮጵያ የተከሰቱ ችግሮችን በተለይም የፕሬስ፡ የበጎ አድራጎት ድርጅትና እንዲሁም የፀረ ሽብርተኛነት ሕጎችን ይዘታቸውንና ሀገር ወዳድ በሆነው ክፍል ላይ የሚያስከትሉትን አንደምታዎች በመዳሰስ ለውይይት የሚጋብዝ መፍትሄዎችን ያዘለ ሀተታ ቀርቧል። አስተያየታችሁን ብትሰጡበትና ብታዳብሩትም መልካም ይሆናል።

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ(ኢሕአፓ) የመከላከያና የኤኮኖሚ ፖሊሲዎቹ ምን ይዘት እንዳላቸውና ማወቅና መረዳት ለሚፈልጉ አንባቢያን በዝርዝር የሚተነትኑ ሁለት ፁሁፎች በዚህ ዕትም ተካተዋል።

አዕምሮ በለጠ ከአዲስ አበባ የወያኔ የጅምላ አባላት ምልመላ የመጨረሻው የሀገር ማጥፋት ተልዕኮው ማስፈፀሚያ መሆኑን ማጤን ይገባል በሚል ርዕስ የወቅቱን የኢትዮጵያንና የመለስ አገዛዝ ይዞታን የሚተነትን ፅሁፍ ነው። አንባቢያን በቅርቡ በግንቦት 2002 ዓ.ም. ይደረጋል ተብሎ ከሚጠበቀው የመለስ አገዛዝ የምርጫ ተውኔት ጋር ተገናዝቦ ፁሁፉ ቢጠን በርካታ ነጥቦች የበለጠ ግልጽ ይሆናሉና ሀገርን ማዳን አላማው ላደረገ ግለሰብም ሆነ ድርጅት አይኑን ጣል አድርጎ ሊያነበው የሚገባ ነው።

ከፍኖተ ዴሞክራሲ የተገኙ ወቅታዊ ሀተታዎችንም አካተናል። በተለይም ስለወያኔ እኩይ ድርጊት ከሚተነትነው አንስቶ ይህንን አገዛዝ ለማስወገድ ምን መደረግ እንዳለበት አጠር ባለ ደረጃ የሚጠቁም የታክቲክ ስልቶች ያካተቱ ናቸውና ከሕዝብ ወገን መሆን ለሚፈልግ ሁሉ ሊያውቃቸውና በተግባርም እየፈተነ ሊዳብሩ የሚችሉ በመሆናቸው የቅርብ ግንኙነትና የሃሳብ መጣጣም ካለ የትግል ጓደኛ ጋር በመወያየት የመለስ አገዛዝን ለማስወገድ በሚደረገው እንቅስቃሴ ጠቃሚ መሆናቸው ብዙዎች የሚስማሙበት ነው።

ሀገር በቀል ከሆነውና ከፍተኛ አድናቆትና ድጋፍን በኢትዮጵያዊያን፡ እንዲሁም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቀናኢ በሆኑ ሰላም ወዳድ ኃይሎች ጭምር እያተረፈ ከሚገኘው የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ(ኢፖእአኮ) ይፋ ካደረጋቸው መግለጫዎቹ ጠቃሚ ጥቅሶችንና እንዲሁም ስደተኞችን አስመልክቶ ለደቡብ አፍሪካ መንግስት ፕሬዘዳንት ያቀብ ዙማ፡ እንዲሁም ለኖርዌይ ሀገር ባለሥልጣናት የተላኩ ግልጽ ደብዳቤዎች አቅርበንላችኋል። ለኢትዮጵያዊያን ስደተኞች መብትና ጥቅም እንዲከበርላቸው፡ ደህንነታቸውም እንዲጠበቅላቸው የተቻላችሁን አስተዋጽዖ ለማበርከት መነሾ ይሆናችኋልና በጥሞና ተመለከቱት።

በመጨረሻም 9/11 በሚል የሚታወቀው የአጥፍቶ ጠፊዎች ሽብር ድርጊት በኋላ አሜሪካ ሽብርን ለመከላከል በሚል በአፍሪካ አህጉር ለማስፈር ስላደራጀችው አፍሪኮም የዕዝ ጦር ኃይል ተቋም ለዳግማዊ ቅኝ አገዛዝ መሳሪያ ነውን? በማለት የተቹበትን የትንተና ሃሳብ ያካፍሉናል።

አንባቢያን እንደተለመደው በፍካሬ ውስጣዊ ይዘቷም ሆነ ባቀረበችው መጣጣፎች ላይ ያላችሁን አስተያየት ብትልኩልን በደስታ እናስተናግዳለን። በሚቀጥለው እትም እስከምንገናኝ መልካም ንባብ እንመኝላችኋለን።

# በ2009 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የተከሰቱ ችግሮችና መፍትሄ ተብለው የተወሰዱ እርምጃዎች ያስገኙት ጥቅምና ያስከተሉ ጉዳቶች !!

ከኃይሉ ወንዴ

በአለፈው በፈረንጆች በ 2009 ዓ.ም. በአለም ላይ በርካታ አሉታዊ ክስተቶች ታይተዋል። ለአብነት ለመጥቀስ ያህል ከተፈጥሮ ችግሮች መካከል ዋናዎቹ የአሳማ ጉንፋን ወረርሽኝ፡ ድርቅ፡ ማዕበልና የመሬት መንቀጥቀጥ እንዲሁም ከሰው ሰራሽ መካከል ደግሞ በግሎባላይዜሽን አማካኝነት በኤኮኖሚ በዳበሩት ሀገራት ውስጥ ከፍተኛ የገንዘብ ቀውስ (financial crisis) መፈጠርና ያስከተለው የስራ አጥነት፡ የገንዘብ ዋጋ መጋሸብና የትናንሽ ሀገራት አምባገነን መሪዎች በሀያላን መንግስታት ድጋፍ መጠናከር ሲሆን የኪዮቶ ውልን ይተካል ተብሎ የተገመተው የኮፐንሃገን የአየር ብክለትን የመቀነስ/የመገደብ ጉባኤ ከስምምነት ላይ አለመድረስ የመሳሰሉት ይገኙበታል። እነዚህ ችግሮች በተለያዩ ገጽታቸው በፖለቲካ ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች ላይ ተጽዕኖ ማሳደራቸው የማይቀር መሆኑ ደግሞ ግልጽ ነው። በዚህም የተነሳ በከፍተኛ ደረጃ በተከሰተው የኤኮኖሚ ድቀት፡ የአካባቢና አየር መዛባት በመሳሰሉት ፈተኛ የሆኑ ክስተቶች አለም ተወጥራ የምትገኝበት ሁናቴ በመኖሩና ኢትዮጵያም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የነዚህ ችግሮች ቀማሽ በመሆኗ ሁላችንንም አጥብቆ ይመለከተናልና አጠር ባለ ሁናቴ መዳሰሱ መፍትሄ ለማግኘት ይረዳልና አግባብነት ያለው ይሆናል።

ብዙ እርቀን ሳንሄድ በአፍሪቃ ቀንድ አካባቢ በጎረቤት አገሮች ሰላም መጥፋትና አለመረጋጋት፤ የወያኔ አምባገነን አገዛዝ በሱማሊያ የርስ በርስ ብጥብጥ ውስጥ ጣልቃ መግባትና ወረራ ማካሄድ በሕዝባችን ሰላምና ብሔራዊ ደህንነት ላይ እያስከተሉ ያሉት መዘዞች በዋቢነት የሚጠቀሱ ናቸው። በመጭው 2010-2011 ዓ.ም. በሱዳን የሚደረገው ብሄራዊ ምርጫና የደቡብ ሱዳን ከሰሜን ሱዳን ጋር አብሮ በአንድነት መቀየት ወይም እራሱን የቻለ ነፃ አገር የመሆን ብይንተ ሕዝብ የተለያዩ ችግሮችን በውስጡ ቀፍቅፎ የያዘና ውጤቱ ምን እንደሚያስከትል ለመተንበይ እያስቸገረ ያለው ሁኔታ ሌላው የሚጠቀስ ምሳሌ ነው። ለማንኛውም የእኛ ግምገማ ዋና ትኩረት ግን ሁሉንም ክስተቶች ከግንዛቤ በማስገባት በአለፈው አመት ከተፈጥሮ ችግሮች ባሻገር በሀያላን አገሮች በተለይ አሜሪካ፤ እንግሊዝ፤ ጀርመንና ሌሎችም እርዳታና ትብብር በዘረኛው የመለስ አገዛዝ አማካኝነት በሕዝባችን ላይ የተፈጸሙ የፖለቲካ፡ የኤኮኖሚና የማህበራዊ ቀውሶች ያደረሱትን ጉዳቶችና ለመጭው አመታት የሚያስከትሉትን እንደምታዎች በአጭሩ ለመተንተንና መፍትሔዎች ይሆናሉ ብለን የምናስበውን ሀሳቦች ለመጠቆም ነው። ይህ መሰረቱና እይታው ጎጠኛ የሆነ አምባገነን አገዛዝ በአስራ ስምንት አመት የሥልጣን ዘመኑ የፈጸመውን እኩይ ተግባራትን በመዘርዘር አንባቢን ለማስልቸት ሳይሆን የአመታት የቀውስ ድምር ውጤቶችን በማሳየት አሁን ይህ ጽሁፍ በሚዘጋጅበት 2009 ዓ.ም. መጨረሻ ላይ የደረስንበትን የፖለቲካ፡ የኤኮኖሚና የማህበራዊ ችግሮቻችን ለመመርመር፡ ከነዚህ ጋር በተያያዘም በተቃዋሚ ጎራ ውስጥ የተከሰቱትን ውዥምብሮችና ትርምሶች በሁለንተናዊ መልካቸው መዳሰስ ሌላው የዚህ መጣጥፍ ዋና አላማ ይሆናል።

## የፖለቲካ ቀውሶችና እንደምታቸው

ሁላችንም እንደምናውቀው ሁሉ የወያኔ አምባገነን አገዛዝ በ1991 ዓ.ም. ሥልጣን እንደጨበጠ የራሱን የፓርቲ የፕሮግራምና መርሃግብር በማንአለብኝነት የአገሪቱ ሕገ መንግስት በማድረግና አገራችንን ያለ ምንም ጥናትና ሕዝባዊ ይሁንታ በቋንቋ ላይ ብቻ በመመስረት በተለያዩ ክልሎች በመሸንሸን በሕዝባችን ላይ የፈጸመው በደል ብዙ የተነገረለትና የተባለለት ጉዳይና እልቆ መሳፍርት በመሆኑ ወደዚያ ዝርዝር ውስጥ መግባት አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም። በበኩላችን ማተኮር የምንፈልገው በአመታት የተከማቹ ችግሮች ላይ የምርና የጠለቀ ውይይት ለመጋበዝና ተጨባጭ የሆነ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በመፍጠር ከገባንበት አሳሳቢና አሳዛኝ ቀውስ በአሸናፊነት የምንወጣበትን መንገድ በጋራ ለማፈላለግ ነው።

ወያኔ እንደ ድርጅትና ሕዝባዊ ይሁንታ ያላገኘ አገዛዝ ከ97ቱ ዓ.ም. የምርጫ ሽንፈቱ ከደረሰበት ቅሌትና ስህተቱ ትምህርት በመውሰድ የስልጣኔ ተቀናቃኝ ናቸው የሚላቸውን ተቃዋሚ ድርጅቶችን ለማዳከምና ለመከፋፈል እንዲሁም ሕዝብን ሊያንቀሳቅሱ የሚችሉበትን ቀዳዳዎች ሁሉ በመድፈን ላለፉት አራት አመት ሙሉ ሲሰራ ባጅቷል። በአንጻሩ የተቃዋሚው ጎራ ስህተቱን አርሞና ተጠናክሮ በመውጣት ፋንታ ከመቼው ጊዜ በባሰ ውዥምብርና ትርምስ ውስጥ ተዘፍቆ የሚገኘው የዚሁ ተግባር ውጤት በመሆኑ ጥረቱ አልተሳካለትም ማለት አይቻልም። እንደአለፉት አመታት ሁሉ ትግሉን ማን ይምራው? ድርጅት ወይስ እንቅስቃሴ? ምን ዓይነት ትግል? ሰላማዊ? የትጥቅ ትግል? ሁለገብ ትግል? ለመታገል ቅንጅት/ህብረት ወይስ ጥምረትና ትብብር ነው የሚሻለው በሚሉ አሰልቺና አንዲትም ስንዝር የሕዝቡን ትግል ወደፊት በማያራምዱ ውይይቶች ተቸብችቦ መገኘቱ የሚያመላክተው ይህንኑ መሆኑ ለሕዝብ ቀናኢና ሀገር ወዳድ ለሆኑ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ከግልጽም ግልጽ ነው።

በእኛ አስተሳሰብ የተቃዋሚ ጎራው በእንዲህ የመሰለ አሳፋሪ ሁኔታ መገኘት ዋናው ምክንያት ወያኔ ጠላት ወይስ ወዳጅ ነው? ለሚለው ወሳኝ ጥያቄ በሚገባ መልሱን ሰጥቶ ለማስረገጥ ያለመቻል ጉዳይ ነው። በርግጥም ከሥልጣን ላይ ያለው የመለስ አገዛዝ ጠላት ነው ከተባለና በዚህ ላይ ከልብ ታምኖበት ቆርጠ ለመታገል መወሰን ከተቻለ ሕዝብ ሊሸከመውና የራሱም አስተዋጽዖ በሚታከልበት በማናቸውም የትግል ስልቶች ሁሉ በመጠቀም የመለስ አገዛዝን ከሥልጣን አውርዶ፣ ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርአት መገንባት ይቻላል የሚል ጽኑ እምነት አለን። የአገርን ጥቅም የመጉዳት ጥፋቶች በጃንሆይም በደርግም የተካሄደ ነውና ወያኔ ለብቻው ተነጥሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት አያሰኘውም እየተባለ የሚቀርበው አስተያየት የወያኔን እውነተኛ ጠባይና በርግጥም ጠላት መሆኑን ሊያድበሰብሱ የሚከጅላቸው ካልሆነ በስተቀር በምንም አይነት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የመጣ ጉደኛ አሪዮስ መሆኑን አይሸፍንለትም። ጠለቅ ብሎ ከታየም ይህ አስተያየት ውሃ የማይቋጥር መሆኑን ከሁሉ በላይ ሕዝባችን በቅጡ የተገነዘበው ነው።

ነገር ግን የትጥቅና ሰላማዊ ትግል እጅግ ተደጋጋፊ መሆናቸውን ወደ ጎን በማድረግ የትጥቅ ትግል ቀራጥ በሆነ፤ የሕዝቡን የልብ ትርታ በሚገባ በሚያዳምጥ የፖለቲካ ድርጅት ካልተመራና ሕዝብም ከልቡ አምኖ ካልተሳተፈበት ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት

አግዝፎ በማየት ብቻ የሰላም ኃዋሪያ ለመሆን የሚደረገው ጥረት የአምባገነን አገዛዝ እድሜን ማራዘሙና ሕዝብም መነሳቀሉ የማይቀር መሆኑ ነው። በተለይም የሰላማዊ ትግልን ትርጉምና ይዘት በማዛባት ወያኔ ወዳጅ ነው ወይም ሊሆን ይችላል ከሚል ከተሳሳተ አቋም በመመስረት የአገዛዙ ተለጣፊ ወይም ታማኝ ተቀዋሚ በመሆን እየተደረገ ባለው እንቅስቃሴ የመሰማራቱ ጉዳይ የዚሁ ነፀብራቅ ነው። ይህ ደግሞ ሕዝብን በግንባር ቀደምትነትና በቆራጥነት አታግሎ ለማታገል እንደማይቻል ቢያንስ ያለፉት አመታት ተመክሮዎች የሚያሳዩት ናቸው። በመለስ አገዛዝ ሙሉ ቁጥጥር ሥር በሚገኘው ምክር ቤት ተብዬ ውስጥ በርጩማ በማግኘት አዝጋሚ ለውጥ ማምጣት ይቻላል የሚለው አስተሳሰብም የዚሁ ውጤት መሆኑ ጥርጥር የለውም። ራሱ ሕግ አርቃቂ፣ ራሱ ከሳሽ፣ ራሱ ዳኛ፤ ራሱ ካለፈው በበለጠ ፈላጭ ቆራጭ ሊያደርገው በቻለበትና የሚቀናቀኑትን እንዳሻው ሊያደርጋቸው በሚችልበት የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ ተስማምቶ መታገል የሚለውም ከዚሁ ከተሳሳተ ሰላማዊ ትግል ግንዛቤ ላይ የተመሰረተ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘም ሁኔታውን ይበልጥ እያወሳሰበ የሚገኘው በእኛ አስተያየት ለውዥምብርና የብዥታው መጠናከር በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ የተሰገሰጉ የወያኔ ቅጥረኞችና እበላ ባዮች ሳይዋጉ ተዋግተን ይህን ያህል ማረክን፣ በዚህ በዚያ እንዲህ አደረግን በማለት የሕዝባችንን ልብ በመስቀልና በማነሁለል በአጉል የቀቢጠ ተስፋ በማወናበድ፤ ገንዘብ መሰብሰብ ላይ የሚገኙት ናቸው። በነገራችን ላይ ይህ ሃቅ የተደበቀው ተቀዋሚ ነን ከሚሉትና ከወያኔ ሳይሆን ከሕዝባችን ነው።

የሰላማዊ ትግል ሃዋሪያን ነን በማለት ሲገዘቱ የነበሩት ክፍሎች ደግሞ ወያኔን ይበልጥ በማጋለጥ የሕዝቡን የትግል እንቅስቃሴ አንድ እርምጃ ወደፊት ያራምዳሉ ተብለው የተገመቱትን ከ97ቱ ምርጫ በኋላ የቀረቡትን ባለስምንት ነጥብ ቅድመ ሁኔታዎች ካሁኑ ሁኔታ ጋር በማዛመድ እንዲሟሉ ምንም አይነት ጥረት ሳይደረግ በመለስ አገዛዝ የቀረበ የምርጫ ስነምግባርና ደንብ ያውም አባሎቻቸውን እንኳ በሚገባ ሳያማክሩ በመፈራረም በ2010 የምርጫ ተውኔት ለመሳተፍ መወሰናቸው ሀገር ወዳድና የአንድነት ኃይል ተብለው በሚገመቱት ክፍሎች መካከል ያስከተለው ውዝግብ ለተቃዋሚ ክፍል መዳከም የበኩሉን አስተዋጽዖ አበርክቷል። በመድረክ ሥር የተሰባሰቡ ድርጅቶችም በቅርቡ በሊቀመንበራቸው በተሰጠ ቃለ መጠይቅ አማካኝነት እንደተገለጸው የምርጫ ስነምግባርና ደንብ ባይፈርሙም ሕግ ሆኖ እስከወጣ ድረስ በምርጫው ለመካፈል በዝግጅት ላይ እንደሆኑ ተገልጿል። በሁለቱ ክፍሎች መካከልም ውስጥ ውስጡን ሲካሄድ የነበረው አሁን ግን ይፋ የሆኑ ልዩነቶች እየተንጸባረቁ መሆናቸው ይታያል። ይህ በበኩሉ የመለስ አገዛዝን ምን ያህል ጠቀሜታ እያስገኘለት እንደሆነ ግልጽ ቢሆንም ይበልጡኑ የሚጋለጥበት ሁኔታ ደግሞ ከምርጫ ተውኔት በኋላ የሚታይ ስለሚሆን በዚሁ ማለፉ ለጊዜው የሚመረጥ ነው።

ይህ እንዳለ ሆኖ ደግሞ በምንም ቢሆን ምን በፍፁም ልንረሳው የማንችለውን ነጋ ጠባ ሊያስታውሱን የሚሹ ኢስፓዎቹም በተለይም በወንጀል የሚፈለጉቱ በየድርጅቶች ውስጥ ሁሉ በመመርመስና በማተራመስ በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ ኢሕአፓን ማጥላላቱና ታሪክን ለመከለስ በመወራጠት ላይ እንደሆኑ እየተስተዋለ ነው። በቀይ ሽብር ተፈላጊ የሆኑ ኢስፓዎች ሀገርና ሕዝብን ለመታደግ የምናደርገው ትግል ክፉኛ ስለሚቀረቁራቸውና ማንነታቸውንም የማንረስ በመሆኑ “የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው” በሚል ጎጂ ብሂል ዘመቻቸውን በዛ ታሪካዊ ትውልድ አባላት ላይ ከአደረጉ ሰነባብተዋል። ይህም በበኩሉ

በመለስ አገዛዝ ላይ ማተኮር የሚገባውን ኃይል በተወሰነ ደረጃ ማዳከሙ የማይቀር በመሆኑ ካለፈው በበለጠ እንዳመጣጣቸው ማስተናገዱና ማንነታቸውን ይበልጥ ማጋለጡ አግባብነት ያለው መሆኑም ግልጽ ነው።

ወያኔ በአለፉት አራት አመታት ከአምስት ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ዜጎችን በማስገደድና በጥቅማ ጥቅም በመደለል በአባልነት መመልመሉን በራሱ አንደበት በተደጋጋሚ የተገለጸ ነው። የራሱን የምርጫ ቦርድ፣ የምርጫ ስነሥርዓት አስከባሪ፣ የምርጫ ድምፅ ቆጣሪና ታዛቢ እንዲሁም የራሱን የበላይነት የሚያረጋግጡ ሕጎች በፓርላማ ተብዩ አፀድቆ ምርጫውን በአሸናፊነት ለመወጣት መዘጋጀቱንም ብዥታ በማይፈጥር ሁኔታ ግልጽ አድርጓል። በማሳረጊያም ለተቃዋሚ ድርጅቶች ምንም ቀዳዳ ላለመተው በአገር ውስጥ በሰላማዊ ትግል እየተንቀሳቀስን ነን ከሚሉት ከመኢአድና ሌሎች 64 ድርጅቶች ጋር የምርጫ ሥነስርአትና ደንብ ስምምነት አግኝቷል በማለት ይህንንም በምክር ቤት ተብዬ አጸድቆ ሕግ ሲያደርግ በመድረክ ሥር የተሰባሰቡት ደግሞ ይህንን ሕግ እናከብራልን ቢሉም መሰረታዊ ቅራኔ እንዳላቸው በመግልጽ በሁለቱ ጎራዎች መካከል የእርስ በርስ ሽኩቻ እንዲኖር ከፍተኛ አስተዋጽዖ አበርክቷል። በተለይም ይህ ውዝግብ ብዙ አባላትና ደጋፊ አለው ተብሎ የሚወራለትን የመኢአድ አመራር ለመለስ አገዛዝ ዋና የፖለቲካና የኤኮኖሚ ድጋፍ ሰጪ በሆኑ ባዕዳኖች አቀናባሪነትና ተባባሪነት በሾኬ ጠልፎ እጉያው ካስገባ ጀምሮ ቀጣይ ሆኖ ይገኛል።

መድረክም ከወያኔ ጋር ለብቻ ለመደራደር ያቀረበው ሃሳብ ውጤት አልባ በመሆኑ የወያኔን ሕግና ስርአት ተቀብሎ ምርጫውን እንደሚካፈል ተረጋግጧል። ለዴምራሲያዊ ምርጫ መሳካት መሰፈርት ሊሆኑ የሚችሉ የተለያዩ ወሳኝ ነጥቦች ባለተሟሉበት ሁኔታ ማዕቀብና በምርጫው አለመካፈል አማራጭ የትግል ስልትና የማንኛውም ዜጋ የማይገሰስ መብት መሆኑን ቢያውቁም ይህንን አማራጭ ግን በአሁኑ ወቅት እንደሚታየው አንግቦ በቆራጥነት ሕዝቡን ለማታገል የደፈረ ማንም ድርጅት የለም። የመንፈስ ጥንካሬና ወኔው ስለጠፋ አቋራጭ መንገድ ሆኖ ያገኙት ከስር ነቀል ለውጥ ትግል ይልቅ አዘጋሚና ጥገናዊ ለውጥ መከተልን ነው።

ዘረኛው የወያኔ አምባገነን ቡድን የስልጣን ዘመኑን ለማራዘም እስካሁን ድረስ ጠንክሮ ከመስራት አልተዘናካም። ቦዝኖም እንደማያውቅ ቢያንስ ያለፉት አራት አመታት በግልጽ የሚያሳዩ ናቸው። በመሆኑም ለሚስራው እኩይ ተግባራት ህጋዊ ሽፋን ሊያስገኙለት የሚችሉትን ማናቸውንም ሕጎች በፓርላማ ተብዬው እንዲጸድቁ አድርጓል። እነሱም የሲቪል ማህበረሰቦች፣ የፕሬስና የጸረ ሽብር ሕጎች ሲሆኑ ከዚህ በታች ባጭሩ እንዳስ ሳቸዋለን።

## *የፕሬስ ሕግ፦*

ይህ ሕግ የሚያነጣጥረው በግል የነፃ ጋዜጠኞችና አሳታሚዎች ላይ ነው። ወያኔ የነፃ ፕሬስ አባላት በ97ቱ ምርጫ ወቅት የተጫወቱትን ሚናና ለሕዝባዊ ትግሉ መጎልበት ያበረከቱት አስተዋጽዖ በሚገባ ተረድቷል። በመሆኑም እነኝህ ጋዜጠኞች በነፃ በአገሪቱ ውስጥ እንደልብ ተዘዋውረው መረጃ እንዳይሰበስቡና ሕትመታቸውንም ለሕዝብ ለንባብ እንዳያበቁ መገደብ ዋና ተልኮው ነው። ህጉም የተዘጋጀውና ጋዜጠኞችን የሚከሰው

ወይም አፍ የሚያዘጋው ማለት በፀረ-ሀገር አንድነትና ሉአላዊነት ቀስቃሽነት፣ ስላምንና መረጋጋት የሚፃረር፣ በአገር ክህደትና ብሄረሰቦችን ለማጋጨት የሀሰት መረጃ በማስራጨት ጽፋችኋል በሚል የሚከስና ለሞት ቅጣትና ለእስራት የሚዳርግ፣ በፍርድ ቤት የሚያንገላታና ከአቅማቸው በላይ የገንዘብ መቀጫ የሚያስከፍልና ዘብጥያ ለማውረድ ሆኖ የተዘጋጀ ነው። በመሆኑም ከእስር የተረፉት/ያመለጡት ጋዜጠኞች ለስደትና ለስራ አጥነት ተዳርገዋል። የመጨረሻው ***አዲስ ነገር*** የተባለው ጋዜጣ አዘጋጆችና አሳታሚዎች ስራቸውን ጥለው ለስደተኝነት መዳረጋቸው የሚያመላክተው ይህንኑ የወያኔ አስጸያፊ ድርጊት ነው።

<u>የፀረ-ሽብርተኝነት ሕግ፡</u>

በአሁኑ ወቅት በተለይ ከመስከረም 11 ቀን 2001 ዓ.ም.(እ.አ.አ.) የአጥፍቶ ጠፊ ድርጊት በኋላ ተቀባይነትንና ተደማጭነትን እያገኘ የመጣው ክስተት ማንናውም ሀገር የሽብር ድርጊትን በግዛቱ በመፈጸም የተጠረጠሩ ሀገር በቀልም ሆኑ ባዕዳን በቁጥጥር ሥር አውሎ የፍርድ ቤት ክስ በመመስረት ጥፋተኝነታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርቦ እንዲቀጡ በማድረግ ሕግን የማስፈጸም፤ የዜጎቹን ደህንነት መጠበቅና የአገሩን ህልውና ማስከበር እንዲሁም ብሄራዊ ጥቅሙን የማስጠበቅ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። ሆኖም በፅንስ አሳብ ደረጃ ሽብርተኛነት ምን ማለት እንደሆነ፤ ሽብርተኛ ማን ነው የሚለው አሻሚና አወዛጋቢ በመሆኑ በአለም አቀፍ ደረጃ አንድ አይነት ትርጓሜና ፍረጃ ወይም ግንዛቤ ላይ ለመድረስ አልተቻለም። ለአንድ ጎራ ሽብርተኛ ተብሎ የሚገመተውና የሚፈረጀው ለሌላው የአርነትና የነፃነት እንዲሁም ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ለማምጣት የሚታገል የለውጥ ሐዋርያ ተብሎ ይወስዳል። ታዲያ ይህ ክስተት እንደወያኔ ለመሰሉ አምባገነን አገዛዞች የፀረ ሽብርተኛነት ካባ በመልበስ እናስተዳድረዋለን የሚሉትን የኢትዮጵያን ሕዝብ ስጥለጥ ብሎ እንዲገዛ ማስፈራሪያና መጨፍጨፊያ ለማድረግ እየተጠቀሙበት ይገኛሉ። በዚህም የራሳቸውን ብሔራዊ ጥቅምና ፍላጎት ለማሳካት የሚንቀሳቀሱ ባዕዳኖች ድጋፍ አለተለያቸውም። የመለስ አገዛዝ በሶማሌ ያካሄደው ጣልቃ ገብነትና ወረራ የዚሁ ነጸብራቅ ናቸው።

የመለስ አገዛዝ ጸረ ሽብር ሕግ ብሎ ሽብርተኝነትን የተረጎመበት ሁኔታ በአለም አቀፍ ደረጃ የተጠበቁ መብቶች በቀላሉ እንዲሸረሸሩ በአገሪቱ ለሚንቀሳቀሱ ሀገር ወዳድ የፖለቲካ ኃይሎች ከፍተኛ አደጋ የጋረጠ ነው። ሃሳብን የመግለጽ ነጻነትን፤ ሰብአዊ መብትንና ክብርን የማስጠበቂያ መሳሪያ ከመሆን ይልቅ እሱ እንዳመቸው ሊደፈጥጥ በሚያስችለው መንገድ የተደነገገ መሆኑ በተግባር እየተገለጸ ይገኛል። ሽብርን ለመቋቋም የሚያስፈልገው መመሪያና ሕጋዊ ተቋማት መሰረታቸው ሊሆኑ የሚገቡትን እንደ ዴሞክራሲያዊ ግብረገብ፤ ሪፑብሊካዊነት እንዲሁም የመልካም ምግባር ጸጋ፣ የሕግ የበላይነት እሴቶችን ያደበዘዘ ነው። ይህ ብቻ አይደለም። ሽብርን ለመቋቋም የሚያስፈልጉት የደህንነት ጥበቃ ተቋማትም ሊመሰረቱ የሚችሉበትን የሽብር ትርጉም ሊከተሉ የሚገባቸው ፖሊሲና የጥቃታቸው ኢላማ እንዲዛቡና ባሻቸው እንዲያደርጉ በተለይም በዜና ተቋማትና በሽብር መካከል ስላለው ግንኑነት ምንም አይነት ልዩነት የማያደርግ ሆኖ የተቀመረ ነው። ሽብርን ሳይሆን ተቃዋሚን ለማጥፋት ላይ ያነጣጠረ ለአገዛዙ የስልጣን እድሜ ማራዘሚያና ሕዝብን ለመጨቆን መጠቀሚያ ሆኖ ያለ ነው።

ወያኔ እንደ ድርጅትም ሆነ እንደ መሪዬ ቡድን ለሕዝብ ምንም ዓይነት ፍቅርና ኃላፊነት የማይሰማው ለመሆኑ ላለፉት 19 አመታት ያደረጋችው ድርጊቶቹ የሚመሰክሩበት ናቸውና በዚህ ላይ ብዙም እስጥ እገባና ማስረጃ መደርደር አስፈላጊ አይደለም። አለም ያወቀውን ለመጥቀስ ያህል ወያኔ በጋምቤላ የአኙዋክ ሰላማዊ ሕዝብ ላይ ባካሄደው ጭፍጨፋ ከሺ በላይ ለጠፋው ሕይወት ተጠያቂ ነው። ይህ በዘር ማጥፋት/ማጽዳት (genocide) የሚፈረጅ ድርጊት መፈጸሙ ከሌሎቹ ብሔራዊ ጥፋቶች ጋር ተደምሮ የወያኔ ቁንጮ የሆነው መለስ ዜናዊና ተባባሪ ጓደኞቹ እንደ አቻዎቻቸው እንደ የሱዳኑ አልበሽር በአለም አቀፍ የሄጉ ፍርድ ቤት የሚያስከስሳቸውና በሕግ የሚያስጠይቃቸው ለመሆኑ ሁሉም ሀገር ወዳና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቀናኢ የሆኑ አለም አቀፍ የሰላም ወዳድ ኃይሎች ሁሉ የሚስማሙበት ነው። መቼም የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ፍርድ መስጠቱ አይቀርም የሚል ግምት ነው ያለን።

ለማጠቃለል ወያኔ እራሱ በመንግስታዊ ሽብርተኛነት ተፈርጆ እያለ ያወጣው የፀረ-ሽብርተኛነት ህግ የሚያነጣጥረው ለነፃነት፣ ለሰብዓዊና ለዴሞክራሲ በሚታገሉት የተቃዋሚ ድርጅቶች ላይ ነው። ዋና አላማው ተቃዋሚዎችን ለማዳከም ከተቻለም የአለም አቀፍ ድጋፍ ለማሳጣትና ለመምታት ከቻለም ለመደምሰስ ነው። ይህ ሁሉን ያዥ የጸረ ሽብርተኝነት ሕግ ሰላማዊ ተቃዋሚዎችን ሳይቀር ተጠያቂና እንቅቅስቃሴያቸውን በፍርሃት እንዲገቱ፣ ከሕዝቡ ሊኖራቸው የሚችለውን ትብብርና ድጋፍ በገዛ ፍቃዳቸው እንዲያቆሙ ሊያደርግ በሚችል መልኩ የተዘጋጀና ለመተርጎምም ክፍት የሆነ ነው። ፍርሃትና ጭንቅ ለመዝራትም በነሱ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ሰላዮቹን አሰማርቶባቸዋል። የመለስ አገዛዝ በኢትዮጵያ በሚያካሂዳቸው ተግባራት ለተከሰቱት ፖለቲካዊ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ችግሮች ዋና ተተያቂ በመሆኑ የመፍትሄ ተካፋይ ሊሆን የሚችልበት ምንም አይነት የሞራል ብቃት የለውም። መፍትሄ አቅራቢዎችችና በአማራጭነት ሊቀርቡ በሚችሉ በርካታ ድርጅቶችን ደግሞ ሽብርተኛ እያለ በጦር ለመደምሰስ የሚፍጨረጨር በመሆኑም ችግሩን ይበልጥ እያባባሰው ይገኛል።

*__የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሕግ፣__*

ይህ ሕግ የሚያነጣጥረው መንግሥታዊ ባልሆኑ አገር በቀልና የውጭ አገር ድርጅቶችን እንቅስቃሴዎች በመግታት ስራቸውን በአግባቡ እንዳይሰሩ ለማድረግ የታሰበ ነው። ይህም ከሞላ ጎደል እየተሳካለት መምጣቱ ይታያል። የውጭ አገሮች ወይም አለም አቀፍ ድርጅቶች እንደ ቀይ መስቀል አይነቶቹ በጦርነትና በረሃብ ለተጎዳው ሕዝባችን የእርዳታ አገልግሎታቸውን በተገቢው መንገድ እንዳያቀርቡ ጋሬጣ እየሆነባቸው መምጣቱን ከሚሰጡት ቅሬታዎች መገንዘብ አያዳግትም። የወያኔ ትልቁ ፍራቻ ድርጅቶቹ ከሕዝቡ ጋር ሊኖራቸው በሚችለው ቅርበት ተጨባጩን ሁኔታ፣ ጭንቀትና በደል ለመገንዘብና የመለስ አገዛዝን እኩይ ድርጊት ለማየት የሚችሉ በመሆናቸው ይህንንም በተወሰነ ደረጃ ለአለም ሕብረተሰብ ያጋልጡባናል የሚለው ለመሆኑ መገመት አያዳግትም።

መሰረታቸው ሀገር በቀል የሆኑ እንደ የሴቶች ጠበቃ ድርጅት የተደፈሩ ሴቶችን መብትና ድህንነት የሚከራከሩና ሌሎችም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ ለስራ ማስኬጃ የሚሆናቸውን የሚሸፍኑት ከአለም አቀፍ ማህበረሰብ በሚያገኙት እርዳታ

ነው። በዚህም የተነሳ እነዚህ ድርጅቶች ከባዕዳን የምታገኙት እርዳታ ከኢትዮጵያዊያኑ አስር በመቶ ከበለጠ እንደ ውጭ ድርጅቶች ትመደባላችሁ ብሎ ሕግ ማውጣትና ተግባራዊ ማድረግ የነዚህን ድርጅቶች የመንቀሳቀስ መብታቸውን መቀጨትና ማገድ ነው የሚሆነው። በሌላ በምንም አይነት ሊተረጎም አይችልም። ይህ ብቻ አይደለም። መሰረታዊ መብታቸውንም መግፈፍ ነው። ሌሎች ደግሞ አገር በቀል የሆኑ እናትና አባቶቻቸው በቀሳፊው ኤድስና በሌላ ተላላፊ በሽታዎች ምክንያት ለእጓለ ሙታንነት የተዳረጉ በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠሩ ህጻናትን ባላቸው አቅም ተገቢውን እንክብካቤ ለማድረግ የሚጨረጨሩትንም የሚገድብ ነው። ይህ በንዲህ እንዳለ ደግሞ በሌላ በኩል ከወያኔ ጋር ንክኪና በነሱ ሥር የሚካሄዱ ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦችና ብድኖች እጓለ ሙታንን ብቻ ሳይሆን በድህነት ምክንያት እያሳበቡ ሕጻን ልጆቻቸውን ለጉዲ ፈቻ ሽያጭ መቀፍቀፊያነትና ጣቢያነት እየተጠቀሙባቸው መሆናቸውን የተለያዩ ዘገባዎች ያስረዳሉ።

## *የኤኮኖሚ ቀውሶችና እንደምታቻው*

የኤኮኖሚ ቀውስ ትንታኔያችን ብቻውን እንዲያመችና እንድናተኩር ተደርጎ የቀረበ እንጂ ከፖለቲካው ቀውስ ጋር በቀጥታ የተያያዘና የተቆራኘ ነው። የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ለመሆናቸው ግልጽ ነው። በወያኔ አምባገነን በአለፈው አስራ ስምንት አመት የፈጸመውን ውድመት ለመዘርዘርና የመረጃ አሃዝ/ቁጥር በመደርደር የአንባቢን ጊዜና የጽሁፋችንን ቦታ ስለሚሻማ እንዲሁም ህብረተሰባችን ጠንቅቆ ሁሉንም የሚያውቀው ጉዳይ በመሆኑ አንባቢዎቻችን በሚቻለን መጠን ላለማሰልቸት ለመቆጠብ ጥረት አድርገናል። ዋና ትኩረት ያደረግነው "ምን መደረግ አለበት?" በሚለው ላይ ነው።

የወያኔ የኤኮኖሚ ፖሊሲ እንደማንኛውም ታዳጊ አገሮች ሁሉ የይስሙላ ሲሆን፣ በአለፉት አስራ ስምንት አመታት ሦስት የአምስት አመት ፕላኖች እንዳቀረበና አሁን አራተኛውን የአምስት አመት ፕላን ነድፎ በመጭው ምርጫ አሸናፊ ሆኖ ተግባራዊ ለማድረግ በዝግጅት ላይ ይገኛል። የወያኔ የአምስት አመት ፕላን ዴሞክራሲ ስርዓት ካላቸው አገሮች የአምስት አመት ፕላን ጋር ሲነጻጸር በቅርጽም ሆነ በይዘት በጣም የተለይ ነው። የወያኔው ፕላን የሕዝብ ተሳትፎና ይሁንታ ያላካተተ የውጭ እርዳታና ብድር እዲያስገኝ ሆኖ የተዘጋጀ ነው። የወያኔን ፕላን ስንመረምረው "ዶሮን ሲያርዷት በመጫና ጣሏት" እንደሚባለው ሁሉ የተባለው የልማት እቅድ ገና ሳይጀመር የእድገቱ ውጤት ፕሮፓጋንዳ ቀድሞ በአስር በመቶ እድገት መመዘገብን "የምስራች ምስር ብሉ" የሚያበስር ነው። የሚገርመው በሌለ ምስር ጥዋትና ማታ እራሱ ደንቁሮ የሕዝባችን ጆሮ ማደንቆሩ ስራዬ ብሎ መያያዙ ነው። የወያኔ የገጠርና የከተማ ልማትና እድገት ፖሊሲዎች ተግባራዊነታቸውና ያደረሱትን ውድመትና ጥፋት እንዲሁም ወደፊት የሚያስከትሉን መዘዞች ማለትም እንደምታዎችን ከዚህ በታች በአጭሩ እናቀርባለን።

## *የወያኔ የገጠር ፖሊሲ*

የገጠር ፖሊሲው የአርሶ አደሩን ጥቅም የሚያስከብር ሳይሆን በተቃራኒው ኑሮው የቆረቆዘና ለድህነትና ለረሃብ የተጋለጠ የሚያደርገው ነው። በአጠቃላይ አገሪቱ የምግብ ዋስትና ማለት ትኩረት በአገር ውስጥ በሚበሉ አዝርዕት (food crops) ላይ ሳይሆን

ያለበትን የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለመቀነስ በሚያስገኙ አዝርዕት (cash crops) ላይ እርብርብ የሚያደርግ ነው። የአገራችን ችግርና አበሳ መች በዚህ ይቆማል። በአለፈው በ2009 ዓ.ም. የአለምን ሕብረተሰብ ጉድ ያሰኘው በምዕራብ ኢትዮጵያ የሚገኘውን ዳር ድንበራችን በማስደፈር በአካባቢው የሚኖረውን ሕዝብ ማፈናቀሉ ጉዳይ ነው። ገና ለገና ተቃዋሚዎቼ የሱዳንን ምድር መነሻ በማድረግ ጥቃት ያደርሱብኛል ከሚል ፍራቻ፣ ለም የሆነና ውሃ ገብ መሬታችንን ለሱዳን በገፀ በረከት ከማስረከብ አልፎ፣ በመሃል አገር ደግሞ አርሶ አደሮችን ከመሬታቸው በማፈናቀል ለአረቦች፣ ለህንዶች፣ ለቻይናዎች፣ ለኮርያኖች ለግብጾች እንዲሁም ሌሎች ወደፊት ለሚጠይቁ ባዕዳን ሁሉ በልማት ስም ወያኔ እየቸበቸበና ገና በስፋት ለመቸብቸብም በዝግጅት ላይ ነው። የመዋዕለ ነዋይ አፍሳሾች (investors) ዋና አላማቸው ለአገራቸው የምግብ ዋስትና ማረጋገጥና የተረፈውንም ለአለም ገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ ለመሆን ነው። እነዚህ አዲስ የቅኝ ገዢ ሰፋሪዎች ከኢትዮጵያ ሕዝብና ከአጎራባች አገሮች ጋር ግጭት ውስጥ ይገባሉ የሚል ስጋት አለን። ለምሳሌ ቻይና በአዲሱ ባገኘችው መሬቷ ላይ ሕዝቧን በማስፈርና ይበልጥ ተጠቃሚ ለመሆን የአባይ መጋቢ ወንዞች ለገድባ በመዘጋጀት ላይ ነች። የአባይ ወንዝና የተፋሳሾቹ ሕጋዊ ባለቤት ነኝ ባይዋ እንደ አለፈው ጊዜ ማለት ኢትዮጵያን አንድ ማንኪያ "ያለኔ በፈቃድ ብትነኩ ጦርነት አውጃለሁ" ለቻይና ለማለት ባለመቻሏ ባዶ ማስፈራሪያ የዲብሎማሳዊ ግንኙነት አቋርጣለሁ በማለት በመዛት ላይ ትገኛለች። የዘረኛው የወያኔም አምባገነን "እኔ ከሞትኩ ስርዶ አይበቀል" ዓይነት የውጭ ቅጥረኛ በመሆኑ ምናልባት እንደ ኮፐንሃገን ቅሌት ሁሉ የአፍሪቃን የአባይ ተፋሳሽ አገሮች ያቀረቡትን የፍትሃዊ የአባይ ወንዝ ውሃ የመጠቀም መብታቸውን አሳልሮ ለግብፅ አይስጥም፣ አይስማማም ማለት አስቸጋሪ አይደለም። እንደ ብዙ የልማት ጠበብት አስተያየት ከሆነ ወደፊት በአለም ላይ የውሃና የእርሻ ተስማሚ መሬት እጥረት መከሰትና ተፈላጊነቱ መጨምር በአገሮች መካከል ጦርነት ቀስቃሽ ነው የሚል ግምት እያስተጋቡ ናቸው። ስለሆነም ሁሉንም ነገር በጥሞና መከታተልና መመርመር ለወደፊት ብሔራዊ አንድነትና ደህንነታችን ወሳኝነት አለው እንላለን። ለማንኛውም ወያኔን በስልጣን እንዲቆይ ከፈቀድን የአገር ህልውና ማጣትና ወደ ቅኝ ተገዥነት መዳረጋችን አይቀሬ ነው። ስለዚህ "ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ" እንዳይሆንብን ከወዲሁ ወያኔን አጥብቀን መታገልና ከሥልጣኑ ማስወገድ ዜጋዊ ግዳጃችን የሚሆነው በነዚሁ ምክንያቶች ነው።

*<u>የከተማ ልማት ፓሊሲ፣</u>*

ያንድ ታዳጊ አገር ማለት ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በመግባት ላይ ያለ የአምስት አመት ብሄራዊ ፕላኑ የከተማ ልማትና እድገት ፖሊሲ መሆን አለበት ብለን የምናስበው የከተማውና የገጠሩ ልማት እቅድ ተደጋጋፊና የተቀራኘ መሆን እዳለበት ነው። የከተማው ነዋሪ ዜጎች በአጥጋቢ መልክ የማህበራዊ አገልግሎት ለመጠጥና ለመጸዳጃ ውሃ፣ የኤሌትሪክ ስርጭት፣ ትምህርትና የጤና አገልግሎት በበቂ ማግኘት፣ የመኖሪያ ቤቶች ለሕዝቡ በአቅሙ መጠን ማግኘት እንዲሁም መግስታዊና የግል የሆኑ ስራዎች በብቃትና በፍትሃዊ መንገድ ለሁሉ መዳረስ አለበት ብለን እናስባለን። በወያኔ ዘመን የሆነው ግን የከተሞች ነዋሪዎች ቁጥር መጨመርና አገልግሎቶች መቀነስ እንዲያውም ከነአካቴው መጥፋት ነው። ዋናው ምክንያት ወያኔ ገና ስልጣን እንደያዘ አገሪቱን በዘፈቀደ በክልል በመሸንሸኑና ብዙ ሕዝብ ድሮ አያቶችና ቅድመ አያቶችህ ወደመጡበት ክልል ተመለስ በመባሉ ብዛት ያለው ወደ ከተሞች በመፍለሱ ከተሞች ከሚችሉት በላይ መጨናነቃቸው

ነው። የከተሞች መስተዳድር ውስጥ የተሰገሰጉት ግለሰቦች በችሎታና በእውቀት ሳይሆን በዘመድ አዝማድ የአንድ ብሄረሰብ የበላይነት ለማረጋገጥ የተዋቀረ በመሆኑ ነው። በከተማ አስተዳደር ውስጥም ሙስኝነት፣ ዋልጌነት፣ አድሎኝነትና ዘረኛነት የተንሰራፋበትና የነገሰበት በመሆኑ የስራ መጓተትና የከተማውን ነዋሪዎች የሚያጉላላና የሚያስቃይ ነው።

የነዚህ ሁሉ ቀውሳች ውጤት የስራ አጥነት፣ የኑሮ ውድነትና የገንዘብ ዋጋ መጋሸብ በበርካታው የከተማው ሕዝብ በቀን አንድ ጊዜ እንኳን ምግብ የመመገብ እድል እየተመናመነበት የመጣበት ጊዜ ሆኗል። ወያኔ የገነባቸው ህንጻዎች የካድሬዎቹና የባለሚሎቹ መፈንጫ ነው የሆኑት። የከተማውን ችግር ወያኔ መቅረፍ አቅቶት የከተማ አገልግሎች ለምሳሌ ውሃና መብራት በሳምንት ሁለትና ሶስት ቀን በፈረቃ ነው የሚታደለው። የከተማው ነጋዴም እግር ከወርች ተተብትበው ለወያኔና ለደጋፊ ነጋዴዎች ቦታቸው በኪሳራ በማስረከብ ላይ ናቸው። ከዚያም አልፎ የተቃዋሚ አባል ወይም ደጋፊዎች ናችሁ በመባል እስር ቤት በመታጎር ላይ ናቸው።

_የማህበራዊ ቀውሶችና እንደምታቸው_

የአምስት አመት ብሄራዊ ፕላን በሚነደፋበት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ባለባቸው አገሮች ተመክሮ መረዳት እንደሚቻለው ከፓለቲካውና ከኤኮኖሚው ፓሊስዎች ባላነሰ ትኩረት ይሰጣዋል በተለይም የሶሻል ዴሞክራሲ ተከታይ አገሮች ልዩ ትኩረት የሚሰጡት ጉዳይ ነው። የወያኔው የማህበራዊ ፓሊስ ግን በዘፈቀደ ባወጣ ያውጣው ወይም ይሁነኝ ተብሎ ለጥፋት የተዘጋጀ በመሆኑ የሕዝባችን ኑሮ በገጠርም ሆነ በከተማ ለከፍተኛ ስቃይ የዳረገ ነው። በገጠር የምግብ ዋስትና አለመኖርና በከተማም ለተወሰኢ ጊዜያት በድልድይነት ለኑሮ ዋስትና ሊያገለግል የሚችል (safty net) ከመንግስት ምንም እርዳታ አለመኖር ብዙሃኑን ለምድር ሲኦል ዳርጓቸዋል። የስራ አጥነቱ መበራከትና የኑሮ ውድነት የደሃ ቤተሰብ በቀን አንድ ጊዜ ምግብ በፈረቃ በመብላትና ሕጻናት የተመጣጠነ ምግብ እንጦት ለበሽታ እንዲጋለጡ የሆነበት ሁኔታ በብዛት ተከስቷል። ወጣት ልጃገረዶችም ማለት ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ቤተሰብ ለመርዳት በሴተኛ አዳሪነት በመሰማራት ለኤድስና ለሌላ ተላላፊ በሽታዎች ስለባ እንዲሆኑ ተዳርገዋል። በሃኪም ቤት ተብየዎቹም የዶክተርና የመድሃኒት እጥረት መኖሩ ብዙ በቀላል በሽታ እንዲሞት እየተደረገ ነው። ኤድስ ደግሞ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎቻችንን ለሕልፈተ ሕይወት የዳረገ ብቻ ሳይሆን ወጣቱን ጎልማሳውን አዛውንቱን ባልቴቱን ሳይለይ በደማቸው ይዘው ሕይወታቸውን በጭንቀት እንዲመሩ እያደረገ ይገኛል። በበሽታው ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ ሕጻናት ቁጥራቸው በጣም ከፍተኛ ነው። በሱ ምክንያት ሀገር ተረካቢ የሆኑ የወደፊት ተስፈ ወጣቶች ለውሃ ሽታ ተዳርገዋል። የወደፊት ብሩህ ተስፋ በተወለዱበት ሀገር በማጣታቸው ይበልጡኑ ወደ ድህነት አረንቋ ላለመግባትና የወላጆቻቸው ጧሪ በመሆን ፈንታ ሸክም ላለመሆን ከሀገር ለመውጣት የዘወትር ምኞትና ሕልም ያደረጉ ለጋ ወጣቶች ቁጥራቸው በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ወላጆቻቸውም አርአያ ሊሆኑላቸው አልተቻላቸውም።

የወያኔ ስርዓት ትምህርቱም ልዩ መታወቂያ ስሙ “ትውልድ ገዳይ” የሚባለው ከአንደኛ እስከ ስድስተኛና ከሰባት እስከ አስረኛ እንዲሁም አስራ አንድና አስራ ሁለተኛ ክፍል ለኮሌጅ መግቢያ መዘጋጃ (preparatory) ሆኖ በመዋቀሩ ከትግራይ ክልል በስተቀር

በመደረጉ ጥራት ያለው ትምህርት መስጠት አልተቻለም። እንደ አንድ ተቃዋሚ ድርጅት ሬዲዮ ጣቢያ አባባል *"የእኛ ልጆች ከሰባት እስከ አሰረኛ ቴክኒካል ትምህርት በመሰጠት ፈንታ የሚማሩት ፀጉር መቁረጥና ኬክ መሰራት ነው"* ሲል ዘግቧል። ዩኒቨርስቲ የሚደርሱት አሁን በቅድሚያ የወያኔ አባል መሆን ግዴታ የሆነባቸው መጥቷል። በርካታ ዩኒቨርስቲዎችም ተመስርተዋል ተብሎ ቢለፈፍም የተሟላ የትምህርት መጻሕፍትና መሳሪያ እንዲሁም አስተማሪዎች የሌሉባቸው በመሆናቸው ጥራታቸውን የጠበቁ አይደሉም።

ወጣቶች በለጋ እድሜ ከአሰረኛና ከዚያም በላይ ትምህርት ጨርሳችኋል በመባል በስራ አጥነት ምክንያት ወደ መጥፎ ባህሎች ጫት ቃሚነትና ዋልጌነት በመሰሉ እንዲሁም ወደ ሌላ ወንጀል ስራዎች እንዲሰማሩ ይገፋፋሉ፥ ይገደዳሉ። የዘወትር ምኞታቸውና ህልማቸው ከአገር መውጣት ነው። በተለይም ከአሜሪካና ከአውሮፓ ወደ ኢትዮጵያ አዘውትረው የሚመላለሱ ግለሰቦች ችግራቸውን በጉያቸው ደብቀው አሜሪካና አውሮፓ ገንዘብ በአካፋ እንደሚዛቅ አድርገው በማውራታቸው ወጣት በሙሉ "አሜሪካና አውሮፓ ወይም ሞት" በሚል መፈክር በማንገብ በስሃራ በርሃ፥ በየመን ባህረ ሰላጤና በእስራዔል ድንበር በግብፅ ወታደሮች የሚሞቱን ለአገራቸው ስንት ስራ መስራት የሚችሉ ለጋ ወታቶችን ቤታቸው ይቁጠራቸው ማለቱ ይቀላል።

ሌላው የወያኔ ደላላዎች ወጣት ልጃገረዶችን በማታለል አረብ አገር በጥሩ ደሞዝ እንስቀጥራችኋለን በማለት የሚደርስባቸው ስቃይና ስቀቃ እጅግ ዘግናኝ መሆን ነው። በተለይ በሊባኖስና በዱባይ የሚቀጠሩት ቀጣሪዎቻቸው ፓስፖርታቸውን በመንጠቅ ያለክፍያ ረጅም ሰዓት እንደ ባርያ እንዲሰሩና ከቤት እንዳይወጡና ከሰው እንዳይገናኙ ተጸዕኖ ያደርጉባቸዋል። በቀጣሪዎች አባወራም ያለፍላጎታቸው ይደፈራሉ፥ በአባወራዎቹም ሚስቶች በሚደርስባቸው ድብደባና ስነልቦናዊ ድቀት ራሳቸውን ከፎቅ እየወረወሩ ህይወታቸውን እንዲያጠፉ ይገደዳሉ። የኢትዮጵያ ኢምባሲዎችም ዘወር ብለው አይመለክቷቸውም ለችግራቸውም አይደርሱላቸውም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በመንፈሳዊ አገልግሎት ደረጃ የሃይማኖት መሪዎች ቦታ ማለት የክርስቲያንና የእስልምና አባቶች መሪነት በወያኔ አባላትና ተለጣፊዎች በመሞላቱ ምዕመናን በሰላም ፀሎት ማድረግ የማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል። ከዚያም አልፎ በወያኔ ካድሬዎች ጠብ ጫሪነት ለዘመናት ተከባብሮና ተፋቅሮ የኖረውን የሁለቱን ሃይማኖት ተከታዮች እንዲጋጬና ደም እንዲቃቡ እያደረገ ነው። በአጠቃላይ የማህበራዊ ቀውሶች ከጊዜ ወደ ጊዜ መባባስ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል።

*ማጠቃሊያ፦*

ጽሁፋችንን ለማጠቃለል በአለፈው አመት በ2009 የተከሰቱትን ጎጂና መልካም ነገሮችን በአጭሩ በሁለት ክፍሎ ማቅረብ የሚቻል ነው።

<u>*የተከሰቱ ጎጂ ነገሮች*</u>

ከመቼው ጊዜ በባሰ የሰብአዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች መደፍጠጥ ማለት በዘረኛው ወያኔ አምባገነንና በተለጣፊዎች በአማራው፣ በኦሮሞ፣ በደቡብ ሕዝብ በአጠቃላይ በመላ ሕዝባችን ላይ የሚደርሰው መከራና ስቃይ፤ እስርና ድብደባ እንዲሁም መፈናቀል፣ ግድያና ስደት የመሳሰሉት መባባስ በአለፈው አመት ታይተዋል።

- የፖለቲካ እስረኞች ጉዳይ ምላሽ አለማግኘት የፀጋዬ ደብተራውና የአበራሽ በርታ እንዲሁም ጓደኞቻቸው ደብዛ እንደጠፋ መቅረት። የነአቶ አበራ የማነዓብ የሰላም መልክተኛ አሁንም ድረስ በእስር መሰቃየት እንዲሁም የወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ያለአግባብ ዳግም ለእስር መዳረግ። በ97ቱ የምርጫ ምክንያት የሕዝብ ድምፅ ይከበር ያሉ ከ35ሺ በላይ የሚሆኑ ወጣቶች በዴዴሳና በሸዋ ሮቢና በሌሎች ቦታዎች በስቃይ ላይ መገኘት እንደቀጠለ ነው።

- የስደተኞች ጉዳይ በጣም አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል። ስደተኞች በየመን፣ በግብፅና በሊቢያ እንዲሁም በአጎራባች አገሮች የወገን ያለህ ድረሱልን የሚል ጩኸታቸውን በማሰማት ላይ ናቸው። የኢትዮጵያ ስደተኞች ከረጅምና አደገኛ የባህር ጉዞ በኋላ የመን ሲደርሱ እንደሚታሰሩና ወደ ኢትዮጵያ ያለፈቃዳቸው እንደሚመለሷቸው ይታወቃል። በግብፅ ድንበር በኩል ወደ እስራዔል ለመግባት በሚሞክሩ ኢትዮጵያዊና ኤርትራዊ ወጣቶች በግብፅ ወታደሮች መገደል ከጊዜ ወደ ጊዜ መበራከቱ አሳሳቢ ሆኗል። ኑሯችን ይሻሻል ይሆናል በሚል ከሊቢያም ሆነ ከሌላ ወደ ተለያዩ የአለም ሀገራት ሲባዝኑ በየጫካው፣ በየበረሃውና በየባህሩ ሞተው የቀሩ ዜጎቻችን ቁጥራቸው በቀላሉ የሚገመት አለመሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ወደ ሶማሌላንድ የተሰደዱት ኢትዮጵያዊያን ቁጥራቸው እየጨመረ መሄድ ብቻ ሳይሆን በተለይ እናቶች ከሕፃናት ልጆቻቸው ለመንገድ አዳሪነትና ለከፋ ችግር መጋለጣቸውን መስማቱ ሕሊናን የሚሰቀጥጥ ነው።

- የኮፐንሃገን ጉባኤ ሁሉም አገሮች የሚስማሙበትና የሚገዙበት ሰነድ/ውል ሳይሆን ወደ ፖለቲካዊ ቅሌት ተቀይሯል። የስብሰባው ተካፋይ ቡድኖች ማለት ጂ8 የበለጸጉ አገሮች እንደ አሜሪካን፣ እንግሊዝን፣ ፈረንሳይንና ጀርመን ወዘተ፣ ጂ20 በመካከለኛ ደረጃ የሚገኙ አገሮችን እንደ ህንድ፣ ቻይና፣ ብራዚልና ደቡብ አፍሪቃ የመሳሰሉት አገሮችና ጂ-77 ደሃ አገሮች እንዲሁም የአፍሪቃ አገሮችን የሚወክል በመለስ ዜናዊ የሚመራ ቡድን ነበር። መለስ ዜናዊ የአፍሪቃ አገሮች ከሰጡት ውክልና ማለት የአይር ሙቀት አንድ ዲግሪ ሴንቲግሬድና ጫካዎችን እንደገና ለማልማት የአራትመቶ ቢሊዮን ዶላር ካሳ ከሚጠይቅ ውጭ በጂ8 ከበለፀጉ አገሮች ጋር በግል በመመሳጠር የአየር መቀት ገደቡ ወደ ሁለት ዲግሪ ሴንቲግሬድና የካሳው ክፍያም አስር ቢልዮን እንዲሆን ከሃያላን ጋር ተስማምቶ በመድረክ ብቅ አለ። ይህ አድራጎት የአፍሪቃ አገሮች ጥቅም በሚጎዳና የብዙ ሕዝብ እልቀት የሚያስከትል ነው በማለት ብዙ ጠበብቶችና ተመራማሪዎች አውግዘውታል። የመጨረሻው የውሳኔ አሳብ በሚሰጡበት ጉባዔ ቀን ወደ ስብሰባው እንዳይገባም ታግዷል። እንደ አንድ የጂ77 የድሃ አገሮች ተወካይ የአስር ቢልዮን ዶላር ካሳ “በአደጋው ለሚሞቱ አፍሪቃውያን የመቃብር ሳጥን መግዣ እንኳን አይበቃም” ብለዋል። አንድ ሌላ ታዋቂ የእንግሊዝ ጋዜጠኛ

ደግሞ "አቶ መለስ ለዚህ ውለታቸው ምን እንደሚያገኙ አልተገለጸም" ግን በእኛ በኩል መገመት አያቅተንም። ያለጥርጥር የመለስ አገዛዝ በያዘው የዘረኛ አምባገነን ሥልጣኑ እንዲቀጥል ቡራኬና እርዳታ ማግኘት መሆኑን መጠራጠር አይቻልም።

- የአባይ ተፋሳሽ አገሮች በፍትሃዊ መንገድ በጋራ የአባይን ውሃ የመጠቀም መብት ስምምነት ላይ ለመድረስ ለአመታት ጥናቶችና ድርድሮች ሲደረግ መባጀቱን ሁላችንም የምናውቀው ጉዳይ ነው። አሁን ግን የወያኔ አገዛዝ እንደለመደው እንደ ኮፐንሃገን ሁሉ ከግብፅ ጋር በመሞዳመድ ኢትዮጵያና የአፍሪቃ የአባይ ተፋሳሽ አገሮችን ጥቅም አሳልፎ እንደሚስጥ በብዙ ጠበብቶች እየተነበዩና ውጤቱ ይፋ እስኪሆን እየተጠባበቁ ነው።
- አሳዛኝ ዜናዎች፦ ከልጅነታችን ጀምሮ የምናውቀውና የምንወደው ዝነኛው ድምጻዊ ጥላሁን ገሰሰ እንዲሁም ተውዳጅነት በአገር ባህል ዘፈኖች በአጭር ጊዜ ዝናን የገኘችው የማናልሞሽ ዲቦ አረፍት ነው። እግዚአብሔር ነፍሳቸውን ይማር ለልጆቻቸው፣ ለዘመድ አዝማዱና ለቤተሰባችው እንዲሁም ለወዳጆቻቸው በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የአዘናችሁ ተካፋይ መሆናችንን እንገልጻለን። ዝናን ያተረፉ ድምጻዊያንም ሰልፋቸውን የኋላ ኋላ ከወያኔ ተርታ ያደረጉም አልጠፉም።

*<u>የተከሰቱ መልካምና አበረታች ነገሮች</u>*

- በአለፈው በ2009 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል እንቅስቃሴዎች አካል የሆነው ስነ ጽሁፍና ፊልም በአለም አቀፍ ድረጃ እውቅናን ማግኘት ከመልካም አበረታች ዜናዎች መካከል አንዱ ነው። የሰብአዊ መብት ተሟጋች የሆኑት የአቶ አሊ ሁሴን "የትውልድ ትውስታዎች" ፊልም በዓለም አቀፍ አድናቆትና ሽልማቶች በማግኘት ላይ ነው። ይህ ፊልም ቂም በቀል የሚጋብዝ ሳይሆን የዚያን ትውልድ የትግል ጉዞና ተመክሮ ለአለም ህብረተሰብ በተለይም ለተተኪው ትውልድ በማስተማሪያነት የተዘጋጀ ነው። ከአቶ አሊ እንደተረዳነው ሁለተኛው ፊልም በስራ ውጥን ላይ መሆኑን ነው። ስለሆነም ማንኛውም አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ(ት) ሁሉ መረጃዎችንና ፎቶግራፎችን በመሰብሰብ እንዲሁም በቁሳቁስ በመርዳት መተባበር የሁሉም ሀገር ወዳድ ዜጋ ኃላፊነትና ግዴታ መሆኑን ጠቁሞ ማለፉ ተገቢ ነው።
- በግለሰብ ደረጃ በአርአያነት ከሚጠቀሱት የዴሞክራሲ ታጋዮች መካከል አንዱ የሆነው የህማ ቱማ ስራዎች ማለት ከጻፋቸው በርካታ መጽሐፍትና ግጥሞች መካከል የመጀመሪያው መጽሐፍ "the Socialist Witch Hunt" በብዙ ቋንቋዎች መተርጎምና በተለያዩ በአውሮፓና በአሜሪካን ዩነቨርስቲዎች ውስጥ የስነ ጽሁፍ (literatures) ማስተማሪያነት መጽሐፍ (textbook) ሆኖ መመረጡ አመታት አስቆጥሯል። አሁን ደግሞ በ2009 አመት በዕብራይስጥ ቋንቋ በመተርጎምና በአንድ በታወቀ ዩኒቨርሲቲ በቲያትር መልክ ለሕዝብ እይታ መቅረብ መልካም ዜና ነው። በእኛ በኩል ይህ በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ የደርግ ዘመን ልብ ወለድ መጽሐፍ ወደፊት በመጭው አመታት በፊልም ተቀርጾ

ለሕዝብ እይታ ቢቀርብ ለተተኪው ትውልድ በቅርስነት ጠቃሚ ከመሆኑ ባሻገር ለአለም ህብረተሰብ ትምህርት ሰጭነቱን ትልቅ ግምት የምንሰጠው ነው።

- ኢትዮጵያዊው ፕሮፌሰር ገቢሳ እጀታ በፔርዱ ዩኒቨርስቲ የእርሻ አዝርዕት ተመራማሪ ከሰላሳ አመት በላይ በማሻላ አዝርዕት በአደረገው ምርምር በሽታና ድርቅን የሚቋቋም እንዲሁም ምርታማ የሆነ ዘር ለማግኘት በመቻሉ ከኖቤል ፕራስ የሚወዳደር የእርሻ ሳይንስ ተመራማሪነት የትልቁ ማዕረግ የሎሬት ተሸላሚ ሆኗል። ይኽ የምርጥ ዘር በፍትሃዊ መንገድ ለአፍሪቃ ገበሬዎች በመጠነኛ ዋጋ እንዲያገኙ ከተደረገ በአጭር አመታት ከረሃብ ሊገላገሉ ይችላሉ የሚለው ግምት በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት እያገኘ መምጣቱ መልካም ዜና ነው።

- የአውስትራሊያዊቷ ዶክተር ካትሪን በኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ አገልግሎት በመስጠትና የፊስቱላ ሆስፒታል በመመስረት የስማንያ ስድስት አመት የኖቤል ሽልማት አማራጭ የሆነውን ሽልማት አግኝታለች። ዶክተር ካትሪን በቅርብ ከአረፉት ባለቤታቸው ጋር በመሆን የ32ሺ የኢትዮጵያን እህቶቻችን ሕይወት እንዲስተካከል ረድተዋል። በሰጡት አገልግሎት በብዙዎች ኢትዮጵያዊያን ዘንድ በመልካም አርአያነት ከሚታዩት ባዕዳን ተርታ እንዲታዩም አድርጓቸዋል።

- የሲቪክ ድርጅቶች መጠናከርና መጎልበት በአርአያነቱ መጥቀስ የመረጥነው በቅርብ አመታት የተቋቋመውን የአለም አቀፍ የኢትዮጵያ የሴቶች ድርጅትን ነው። የሴቶች የትግል ተሳትፎ በተለይም የአገራችውን ዳር ድንበርና ነፃነት ሲደፈር ከወራሪ ጠላት ጋር በተደረገው ትግል ሁሉ ከአባቶቻቸው፣ ከወንድሞቻቸውና ከባሎቻቸው ጋር በመሆን መታገላቸውን ታሪክ የመዘገበው ጉዳይ ነው። ግን ይህን አዲሱን የሴቶች ድርጅት ልዩ የሚያደርገው የአለም አቀፍ የሴቶች ድርጅት አባል መሆኑንና በተቋቋመ በአጭር ጊዜ ውስጥ የራሱን ድህረ ገጽና የውውይት መድረግ (paltalk) በመክፈት በሳምንት ሁለት ቀን ቅዳሜና እሁድ በአለም ዙሪያ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንን በፖለቲካ፣ በኤኮኖሚና በማህበራዊ ጉዳዮች በማወያየት በተለይም ሴቶች በፆታ የሚደርስባቸውን በደል ትክክለኛና አግባብ አለመሆኑን በማስተማርና የጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዴሞክራሲ፣ ለነፃነትና ለእኩልነት በሚያደርገው ትግል አካል በመሆን በመሳተፍ ላይ በመሆኑ ነው።

- ሌላ ሳይጠቀሱ የማይታለፉ ነባር ሲቪክ ድርጅቶችን መንዛዛት ካልሆነ ብዙ ሊባልላቸው የሚገባቸው መካከል ጥቂቶቹን እንጠቅሳለን። መመዘኛችን በቅርጽ፤ በይዘት፤ አስተማማኝ መረጃዎችን ለሕዝብ በማቅረብ የምናደንቃቸውን እንደ ደብተራው፣ ኢትዩኤክስና ኢትዮ ላየን እንዲሁም የአሲምባ ድህረገጽና የውይይት መድረክ ማለት የዚያን ትውልድ ታሪክ እንዳይበረዝና እንዳይከለስ የሚከላከል ተቋም በመሆኑ አድናቆታችን ከፍተኛ ነው። እንዲሁም የሐዋሪያ ጋዜጣና በጀርመን የሚታተመው የአደራ መጽሄትም በኢትዮጵያ ማህበረሰ ውስጥ ትልቅ ስርጭት ያላቸው ነባር በመሆናቸው ሊመስገኑና ሊበረታቱ የሚገባቸው ናቸው እንላለን። በተለይ የፖለቲካ ድርጅት ወገንተኝነት ሳያጠቃው ዴሞክራሲያዊና ሰብ አዊ መብቶቻቸው ተገፎ በስደት በእስር ለሚነገላቱ በርካታ ኢትዮጵያዊያን ጠበቃ በመሆን ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያን ራዕይ አንግቦ እስካሁን ድረስ

እየተሟገተ የሚገኘው የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ቀጥልበት በማለት ብቻ ሳይሆን አስፈላጊውን ትብብር ለዚህ ድርጅት ማድረግ ወሳኝነት ያለው መሆኑን መጥቀስ ከአግባብነትም ይበልጥ አግባብነት ያለው ነው።

ለጽሁፋችን ማሳረጊያ እንዲሆን የመረጥነው በ2009 የተቋቋመው የኢህአፓ የወጣት ክንፍ (ኢወክንድ) እንዲሆን ነው። ለእኛ የዚህ ድርጅት መቋቋም የበለጠ ተስፋና ደስታ ሰጪ ነገር የለንም። የእኛን ትውልድ አርማ አንግበው ማለት ከመልካሙ ጎናችንና ከስህተታችን ትምህርት በመቅሰም የትግላችን አላማ ከዳር ለማድረስ ማለት ፍትህና እኩልነት የሰፈነባት ዴሞራሲያዊ ኢትዮጵያን ለመገንባት የተደራጁ በመሆናቸው “ልጆቻችን እደጉ ተመንደጉ” እንላለን።

ርዕሳችን ለመቋጨት ብዙም ሳናስለቻችሁ አንድ የአደራ ማሳሰቢያችን የተደቀነብን አደጋ ለመከላከልና ለማምለጥ የሚችለው ብቸኛው አማራጭ ጠንክሮ መታገል መሆኑን ነው። በሰው ሰራሽ ችግሮች ማለት ረሃብና በሽታ ከማለቃችንና አገራች እንደ አገር ጨርሳ ከመጥፋቷ በፊት እምቢኝ ለአገሬ፣ እምቢኝ ለመብቴና ለነፃነቴ በማለት የወያኔ አንባገነን ስርዓት አስወግደን ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ለመመስረት ትግላችን በሁሉ መስክ እናድርግ። ይህን ካደረግን ብቻ ነው ከታሪክ ተጠያቂነትና በልጆቻችንና በልጅ ልጆቻችን ተወቃሽነት ለመዳን የምንችለው። በትጋት ሁሉን ችግርና መሰናክል በጣጥሰን በአሸናፊነት እንድንወጣ መልካም የትግል አመት እንዲሆንልን እንመኛለን።

„በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ፤ በሁለንተናዊው የሀገሪቱ የፖለቲካ መልከዓ ምድር ላይ በሰፊው ማተኮሩን እንኳ ለጊዜው ጋብ አድርገን፣ በምርጫው ላይ ብቻ እናማትር ብንል፣ በቅድሚያ የምናስተውለው፣ በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተቃዋሚ ኃይሎች አሰላለፍና በወያኔ መካከል ያለውን ሁናቴ ይሆናል። የግንቦቱን ምርጫ አስመልክቶ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከዳር ያለው አቋም የማያወላውል ነው። ይህም በቅርቡ በአዋሳ፣ በጅማ፣ በባህር ዳር፣ በደሴ፣ በአምቦ፣ በአዲስ አበባና በሌሎችም ከተሞች በተጨባጭ የታየ ሀቅ ነው። መጭው የወያኔ ምርጫ ነጻና ፍትሃዊ እንደማይሆንና የተቃዋሚ ድርጅቶችም በዚህ ምርጫ ለወያኔ ሽፋን ሰጪ መሆን እንደሌለባቸው ሕዝቡ በሚገባ አስረግጠ ነግሯቸዋል። ይልቁንም ኅብረታቸውን አጠንክረው ትግሉን በመምራት ለድል እንዲያበቁት በአፅን ዖት አሳስቧቸዋል። የመላውን ሕዝብ አቤቱታና ውሳኔ፣ ተማፅንዖና ፍላጎት መሰረት አድርጎ መታገልና ማታገል ደግሞ ለተቃዋሚ ኃይሎች ዋና ተል ዕኮ ነው። ዘላቂ የሀገር አንድነት፣ የዜጎች እኩልነትም ይሁን፣ ብሔራዊ ጥቅም ሊከበር የሚችለውም፣ የመላ ሀገሪቱን ሕዝቦች ትግል አካትቶ፣ በብሔራዊ ደረጃ መምራት ሲቻል ነው። ይህ ካልሆነ፣ ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት፣ የሀገር አንድነትና ሕልውና ዋስትና ይኖረዋል ማለት ዘበት ይሆናል። እስካሁንም ትግሉ ሁሉ ተሰናክሎ የቀረውና፣ ሕዝቡም ለተፈራራቂ አምባገነኖች አገዛዝ ሰለባ የሆነውም፣ በዚህ ምክንያት ነው። ይህ ክስተት መደገም የለበትም። አዙሪቱ እንዲቀጥል የሚፈልጉት ግን የኢትዮጵያን ሕልውና፣ ጥቅምና የሕዝቧንም አንድነትና ኅብረት የማይፈልጉ ታሪካዊ ባላንጣዎቿ ብቻ ናቸው። ምክንያቱም በዴሞክራሲ የሚተዳደር ሕዝብና ሀገር፣ የቱን ያህል ጠንካራና የማይበገር መሆኑን ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ነው። ዲሞክራሲያዊትና ጠንካራ ኢትዮጵያን ለማየት የማይፈልጉ፣ አገር በቀል ባንዳዎችና ባዕዳን ጠላቶች ለመሆናቸው የሀገራችን ዜና-መዋዕል የመዘገበው ሀቅ ነው።“

*ምርጫ ሲባል ትግል ሰንል ዴምክራሲያ ቅጽ 30 ቁ. 2 የካቲት 1977 ዓ.ም.*

## ለሀገር ሻጭ ዘረኛ ቡድን
## ምንም ምህረት ሊታሰብ አይገባም!!

የወያኔ ቡድን ከ 18 ዓመት ሥልጣን በኋላ ፀረ ኢትዮጵያዊነቱን በግልፅ ለሁሉ ዜጋ ያሳየ በመሆኑ ዛሬም ይህ ቡድን ሀገራዊ ነው፤ ለውይይትና ስምምነት ፅጩ ነው የሚሉ ካሉ ህሊናቸውን የሳቱ መሆን አለባቸው ማለት እንገደዳለን። የመለስ ዜናዊ ቡድን በመስከረም 29 ከሱዳን ጋር ተፈራርሞ የኢትዮጵያን ለም መሬት ለሱዳን ያስረክባል። ይህ የክህደት ክህደት መጨረሻ በመሆኑ ሁሉም ዜጋ ይህን ሀገር ሻጭ ባንዳ ቡድን ለማስወገድ አምርሮ መነሳት አለበት።

የወያኔ መሪዎች ፀረ ኢትዮጵያዊነት በአዲስ ብቅ ያለ በሽታ አይደለም። ገና በናቅፋ ሲመሰረቱና ብሎም ደደቢት ገብተው የመጀመሪያ መርሃ ግብር ወይም ፕሮግራማቸውን ሲያወጡ የለፈፉት የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች እርስ በርስ በቅራኔ የተናከሱ ናቸውና አብረው መኖር ስለማይችሉ ሁሉም ብሄረሰብ ተገነጣጥሎ የራሱን ነጻ መንንግሥት ማቋቋም አለብት የሚል ነበር። በዚህም መሰረት ለነፃ ትግራይ መንግሥት ወይም ሪቱብሊክ እንታገላለን ያለው ወያኔ ትህን ርኩስ ድምዳሜውን የሚቃወመዉን ሁሉ ትምክህተኛ የሸዋ አማራ ብሎም መፈረጁ የሚታወስ ነው። ወያኔ በጋዜጠቹ ትግላችን ፀረ አማራ ነው ብሎ በይፋ ሲጽፍና በዚህ ህዝብም ላይ የዘለፋ ዘፈኖቹን በካሴት ቀርፆ ሲያሰራጭና ኢትዮጵያ ሀገራችን ያሉትን የትግራይ ተወላጆች የአማራ ኮራኩር ወይም ሎሌ ብሎ ሲዘልፍ በመሰረቱ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ትጥፋ ትበታተን የሚል አቋምን ነበር ሲገፋ ሲያስተጋባ የቆየው። ይህንን ዛሬ ለመካድ የሚጥሩ ሁሉ ሀሰትን እያራገቡ ናቸው። የመለስ ዜናዊና ስብሀት ነጋ ፀረ ኢትዮጵያዊነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ ባለመሄዱም ከባዕዳን ጋር በፀረ ኢትዮጵያ ሴራዎች አብረው ሲሰለፉና ሲካፈሉ ቆይተዋል። ሀገር ወዳድ ህብረ ብሔራዊ ድርጅቶችን ማለትም ኢሕአፓና ኢዲኅን ወግተዋል። ተቀናቃኝ ያሏቸውን የትግራይ ነፃ አውጪ ግንባር ወጣት መሪዎችን በአይጋ በድንጋይ ፈጥፍጠውና በጩቤ ወግተው በአሰቃቂ መንገድ ገድለዋል። ከሱዳን ጋር በማበር የደቡብ ሱዳን ስደተኞችን ይዘው ለሱዳን እያስረከቡ በየጥሻው በየመሹሩው አስጨረሰዋል። የኢትዪጵያን የደን ሀብት ዛፋና አርቃዩን ለሱዳን ቸብችበዋል። ኢትዮጵያን እንደ ሀገር የሚጎዱ መረጃዎችን ለባዕዳን ሰጥተዋል። ረሃቡ በገባም ጊዜ የአሜሪካንን ፀረ ደርግ ዕቅድ ለማሟላት ሲሉ የትግራይ ረሃብተኞችን ወደ ወዲ ከውሊ አጓጉዘው በመገድና በኋላም ለእልቂት ዳርገው ስንዴና ገንዘብ በልዋጭ አግኝተዋል። የሐውዜን እርሶ አደር ለደርግ በውስጥ ውስጥ በሰጡት መረጃ መሰረት አስፈጅተዋል። ወጣት የትግራይ አርሶ አደሮችም ለጠመንጃ ልዋጭ በናቅፋ ረግፈዋል። የወያኔ ጸረ ሕዝብ ፀረ ኢትዮጵያ ታሪክ ተዘርዝሮ የሚያቅ አይደለም።

ወያኔ ለሥልጣን እንደበቃ የጎንደርና የወሎን መሬቶች ወደ ትግራይ አጠቃሎ ይዞ እየመዘበረ ነው። ለሥልጣን እንደበቃም ኢትዮጵያን እንደ ባዕድና ክፉ አንበጣ ወራሪ ሆኖ ንብረትና አንጡራ ሀብቷን ወደ ትግራይ አጓጉዟል። ይህን መካድ የሚቻል አይደለም። „ትግራይ እንድትለማ ኢትዮጵያ ትድማ" የመለስና ስብሀት ቀረርቶ ነበር። በአጠቃላይ ዘረና ፖለቲካውን በይፋ በስራ በማዋል የትግራይን ሕዝብ ከቀረው

ኢትዮጵያዊ ለማራራቅና ለማጣላት ዘምቷል። የወያኔ ቡድን ሀ ብሎ ሲጀምር ዘረኛ ነበርና አሁንም በዘረኝነቱ በመቀጠል ኢትዮጵያን የሚያዋርዱ እርምጃዎችን አቋሞችን ሁሉ ቅድሚያ ሰጥቷል። ወያኔን ዘረኛ ስንልም ጥቂር ነጭ በሚል መንፈሱ ሳይሆን ሕዝብን በጅምላ ጠልቶ ሊያጠቃ በመነሳቱና በዘር ወይም ውልደት፤ ቋንቋና ብሄረሰብ ደረጃ አይን አውጣ ልዩነት ለማድረግ ወስኖ በመንቀሳቀሱ ነው። የወያኔ ቡድን ዋና ሞተሩና ማገሩ ኢትዮጵያን እንደ ሀገር መጥላት ነው። ለዚህም ነው ለኢትዮጵያ ጠላት ባዕዳን ሁሉ ሎሌና ታዛዥ የሚሆነው። ለሊቢያ አረብ ነኝ፤ ለግብፅ አባይን በተመለከተ የፈለጋችሁን አድርጉ፤ ለኢራንና ሱዳን ኑና በጥብጡ፤ መሬት ውሰዱ፤ ወዘተ ሲል የቆየው ይህችን ሀገር በመጥላቱ ነው። በአሜሪካ ትዕዛዝ ወደ ሶማሌ ወያኔ ጦር ልኮ ዜጎችን ያስጨረሰውና ኢትዮጵያን በዘላቂው በሚጎዳ መልክ የተንቀሳቀሰው ኢትዮጵያን በመጥላቱ ነው። ነጋ ጠባ የጦር መሳሪያና መሰረታዊ ቁሳቁሶች ወደ ትግራይ መጓጓዛቸው፤ የትግራይ ተወላጆች የንግዱም የትምህርቱም ዋና ተጠቃሚ መሆናቸው፣ የሀገሪቷ ኤኮኖሚ በክልል አንድ ተወላጆችና የወያኔ ደጋፊዎችና አባላት ተቀይዶ መያዙ፣ መበዝበዙ ወዘተ ሁሉ ይህ ዘረኛ ቡድን ምንኛ ፀረ ኢትዮጵያ መሆኑን ያሳያል። ይህን ሀቅ አሌ ማለት የሚቻል አይደለም። ከመቶ ሺ ያላነሰ ዜጋን ለማይረባ ጦርነት ዳርጎ በባድሜና አካባቢው መማገዱና ማስጨረሱም ሀገር ወዳድነት ሳይሆን ሀገር አጥፊ እርምጃ ነበር/ነውም።

በመሆኑም የወያኔ ቡድን የኢትዮጵያን ለም መሬት ለሱዳን ማስረከቡ ስህተት ወይም ድንገተኛ ሳይሆን ከመሰረታዊ ፀረ ኢትዮጵያዊነቱ የመነጨ ነው። ኢትዮጵያ በአምባገነኖች ብትገዛም ከዚህ ቀደም የነበሩት የሀገርን መሬት ለባዕድ የሸጡ አልነበሩም። የሀገርን ለም መሬት ለባዕድ በማስረከብ ወያኔ የመጀመሪያው ከሃዲ ፀረ ኢትዮጵያ ቡድን ነው። ዘረኝነትና ባንዳነት ሳያንሰው ሀገር ሻጭነትንም ተያይዞታል። ይህን ድርጊት በዝምታ የምናየው ሳይሆን አጥብቀን የምንቃወመውና የምንታገለው መሆን አለበት። ወያኔ በያዘው በሁመራ ገፅ ሱዳን የሚፈልገው መሬት ቢኖርም ወያኔ ቅንጣትም ስንዝርም የሚለቅ አይደለም። ቋራን ግን ማስረከቡ አልገደደውም፣ አልከበደውም። ወደ ደቡብም ከጋምቤላ ቆርሶ ሊሰጥ ዝግጁ ነው። የድንበሩን ጉዳይ በተመለከተ ዜጎች በራሳቸው ተደራጅተው ተቃውሞ እንዳያሰሙ በሰርጎ ገቦች አማካይነት እንቅፋትና ጋሬጣ እየዘረጋ መሆኑ ተውቋል። ይህንንም ሻጥር ዜጎች መቋቋም አለባቸው። ሱዳን በአሁኑ ጊዜ በቋራ ነፍሶ ገበያ አካባቢ ጦር ያሰፈረ ቢሆንም ተቆናጠ የሀገራችንን መሬት የራሴ ብሎ እንዳያርስ ማድረግ ማደናቀፍ ይገባል። ይህን ጉዳይ በተመለከተ ተቃዋሚ ድርጅቶች ነን እያሉ ግን ፀጥታና ዝምታን የመረጡ ክፍሎች በታሪክ መጠየቃቸው የማይቀር መሆኑንም ሊያውቁት ይገባል። የቅስቀሳና ተቃውሞአቸው ማዕከል መሆን ያለበትን ይህን ዋና ጉዳይ ችል ብለው በሌላ ያውም ወያኔ በሚሰጣቸው ጥያቄ ላይ ትኩረት ከሰጡ ሀገርና ሕዝብን ይበድላል።

ከሀግርና ለሕዝብ መሬት ሲወረር ወይም በባዕድ ሲያዝ ውርደትና ምፀት ነው። የሀገርን መሬት ለዕብሪተኛ ባዕድ አስረክቦ ዝምታ ሊኖር አይችልም። የመለስና ስብሀት ነጋ ከሃዲ ቡድን በባንዳነትና ውስጥ አርበኝነት ተሰልፎ ኢትዮጵያን ሲያጠቃና ሲያስጠቃ ዜጎች ክተት ብለው መነሳት ይጠበቅባቸዋል። ይህ ጉዳይ ራሱና በራሱ ዋና ነው። የሀገር፣ የመሬት፣ የሉዓላዊነትና ብሔራዊ ክብር ጉዳይ ነውና ከሁሉ ይቀድማል። የአላሙዲ ጉዳይ ቆጠቆተን የሚሉቱ የሀገራችን መሬት ለሱዳን መሰጠቱ አመመን፣ በጠበጠን ብለው

ቢጨሁ የተሻለ ይሆናል። ለዚህም ነው ይህን ዘውረና ፀረ ኢትዮጵያ ቡድን አለምንም ምህረት መታገል የሚገባው። ሀገርን ለባዕድ ከሚሸጥ ቡድን ጋር መሞዳሞድ ሊታሰብም የሚገባ አይደለም። የሚተቃቀፉ ካሉ የወንጀሉ ቆሻሻ እነሱንም የሚነካቸው ይሆናሉ። ከዚህ በተያያዘ ደግሞ የመለስና ስብሀት ቡድን ድርጊት ሁሉ የትግራይን ሕዝብ የነገ ሁኔታ የሚመለከት መሆኑን የትግራይ ተወላጆች ሁሉ ማወቅ አለባቸው። የወያኔን ዘረኛ ፖለቲካ ተቃውመው በኢትዮጵያዊነት አለን እስካላሉ ድረስ ነገ በወያኔ ቡድን ላይ የሚመጣው ዶፍ በነሱም ላይ የሚወርድበት ሁኔታ ሊፈጠርና የማይፈለግ ሁኔታ እውንም ሊሆን ይችላል። የትግራይ ንዑስ ከበርቴውና የተማረው ክፍል ይህን አደጋ በጊዜ ተረድቶ በፀረ ወያኔ ትግል ከቀሪው ኢትዮጵያዊው ጎን ካልቆመ ነገ አይሎ ለሚመጣው የጥላቻ ውጤት ማንም ተጠያቂ ሊሆን አይችልም። በሰፈሩት ቁና የሚለው ዝናብ ሲዘንብ ያኔ ዋይ ዋይታው ጊዜ ያለፈበት ይሆናል። ስለዚህም ከአሁኑና ከወዲሁ ዘረኛውን ቡድን ለብቻው እርቃኑን አጋልጦ ማስቀረትና የጋራ ትግልን መደባለቅ አስፈላጊ ነው። የወያኔ ዘረና ፖለቲካ በቅድሚያና በመጀመሪያ ደረጃ ለአደጋ የሚያጋልጠው የትግራይን ሕዝብ መሆኑን አለመገንዘብ ከባድ ስህተት ይሆናል።

ዘረኛውን ወያኔ እንታገለው።

የሀገራችንን መሬት እናስከብር፤ መዘናጋትና መቸነፍ ያብቃ!!

„መጪው ግንቦት 7 ከመለስ መንጋ ተላቆ እንዲመጣ ከፈለግን ምን ማድረግ እንዳለብን በማያዋላዳ መንገድ ግልፅ መሆን አለበት። አንዱን አምባገነን በሌላ አምባገነን ለመተካት ሕዝብ እቅድ የለውምና በሕዝብ ላይ እንደየማለን የሚሉና ዴሞክራሲንም ለመገደብ የሚከጅሉ ሁሉ መታረም መታቀብ አለባቸው። ተቃዋሚ ኃይሎች ተባብረው በመታገል ሁሉን አቀፍ የሽግግር ሂደትን እውን ለማድረግ መነሳት አለባቸው። ሌላ መንገድ የለም። ያለ ቢመስልም ወደ ውድቀት ወሳጅ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔን እንደጠላ ግልፅ አድርጎ በድምፁ አሳይቷል። ነጻ ሁኔታ ባለመኖሩ ግን ሁሉም ኃይሎች በነጻ ምርጫ ተሳትፈው ሕዝብ የትኛውን እንደሚፈልግ--እንደሚመርጥ ለማሳየት ገና እድሉን አላገኘም። ይህ ነፃ ሁኔታ እንዲከሰት ግን አሁንም በጋራ መታገል መቻል እንደሚገባ ክርክርን አይጋብዝም። ከሀገራችን የፖለቲካ መድረክ የተወሰኑ ወይም የተወሰን ድርጅትን በሰበብ አሳብቦ አግልሎ፡ ከልክሎና ሕገወጥ ብሎ ሰላምን መሻት ከትም የማያዋጣ እርምጃ ነውና ሊታሰብም የሚገባው አይደለም። በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ተወደደም ተጠላም ያሉ ድርጅቶችን በጥሞና ማስተናገድና በሀገራዊ መሰረታዊ ፕሮግራም ዙሪያ ለማሰለፍ ጥረት ማድረግ ይገባል እንጂ መከልከል ማራቅን መምረጡ ያሉትን ችግሮች እድሜ ከመለገስ ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም። በጋራ ትግል የዴሞክራሲያዊው ሽግግርን አማራጭ እውን ማድረግ ያስፈልጋል ማለት ነው።“

መጪው ግንቦት ወያኔ ጥሎ እንዲመጣ
የፍኖተ ሀተታ ---- ግንቦት 9 ቀን 1998 ዓ.ም.

ከትዝብት አድማስ ቁ 84
ጥር 16 ቀን 2002 ዓ.ም.

## ኢሕአፓና የኢትዮጵያ የመከላከያ ፖሊሲ

ኢሕአፓ ከተመሰረተመበት ጊዜ አንስቶ የፓርቲው መሰረታዊ አላማ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይበጃልም ብሎ ባመነባቸው ሀገራዊ ፖሊሲዎች ላይ ቅድሚያና አጽንዖት በመስጠት በደሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ውስጥ ቦታ እንዲሰጣቸው መታገል ነው። በፖለቲካ ፕሮግራሙ ውስጥ አስገብቶ፣ የሚሻሻሉትንም በሂደት እያስተካከለ የትግሉ ማዕከል እንዲሆኑ አድርጎ እስከዛሬ ድረስ በመታገል ላይ የሚገኘውም ለዚህ መሰረታዊ አላማ ብቻ ነው። እነኚህ ሀገራዊ ፖሊሲዎች ግን በተግባር ሊተረጎሙ የሚችሉት፣ በሀገራችን የዴሞክራሲ ሥርአት በአስተማማኝ ደረጃ ሲረጋገጥ ለመሆኑ አሌ የሚባል አይደለም። በፓርቲው የፖለቲካ ፕሮግራም ውስጥ የተዘረዘሩት ልዩ ልዩ ሀገራዊ ፖሊሲዎችን ህያው ለማድረግ የሕዝቡን ሙሉ ነጻነት፣ ሀገራዊ ሉአላዊነትና የሕግንም የበላይነት መሰረት ያደረገ የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ሲመሰረት ብቻ ይሆናል። ሕገ መንግሥትን ያህል መሰረታዊና ቋሚ ብሔራዊ ሰነድ ሕያውነቱን የሚያስመሰክረው፣ በአሳታፊ ዴሞክራሲ የዜጎችን እለታዊ ሕይወት በዕለት ተዕለት በተግባር ሲተረጎም ነው።

መሰረታዊ የሆኑት የሀገሪቱ ዋና ዋና ፖሊሲዎችን አስመልክቶ ለሕዝብ ማሳወቅ የፓርቲው ግዴታውና ተግባሩ በመሆኑ፣ እስከዛሬ ድረስ ሲያደርገው እንደቆየው ሁሉ፤ ዛሬም እንዳስፈላጊነቱ በተከታታይ እየዘረዘረ ያቀርባል። በመሆኑም ዛሬ የምናተኩረው በሀገሪቱ የመከላከያ ፖሊሲ ላይ ይሆናል። በሕዝብ አዎንታ ላይ በተመሰረተ ሕገ - መንግሥት ውስጥ የሚሰፍሩት የሕዝቡን መብቶች የሚያከብር እንዲሁም የሕዝቡን ፍላጎቶችና ጥቅሞች የሚጠብቅ፣ የሀገሪቱንም ድንበርና ሉአላዊነት የሚከላከል የጦር ኃይል፣ የሕዝቡንም ሰላምና ፀጥታ እየጠበቀ ህግና ደንብ የሚያስከብር የፖሊስ ሰራዊት በህግ ማቋቋም፤ ለሀገራችን ነጻነት ዋስትና ነው ብለን እናምናለን። ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ ያላገለለ፤ አስፈላጊ መስፍርቶችንም በሚያሟላ መልኩ ተመልምሎ የተውጣጣ፤ በሙያው የሰለጠነ፣ ታማኝነቱ ለሀገሩና ለሕዝቡ፣ ታዛዥነቱ ደግሞ በሕዝብ ለተመሰረተ መንግሥት የሆነ ብሔራዊ የመከላከያ ኃይል መመስረት የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎት እንደሆነ እናምናለን። የጦር ኃይሉና የፖሊስ ሰራዊት አባላት የሚቀጠሩት በፍቃዳቸው ሆኖ፣ የውዴታ ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ግን ይገነዘቡታል። የጦር ኃይሎችና የፖሊስ ሰራዊት አባላት ሙያቸው በቀን ተቀን ፖለቲካ ውስጥ ጣልቃ ለመግባት ባይፈቀድላቸውምና ደግሞም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለማድረግ የተከለከሉ ቢሆኑም፣ በሀገሪቱ የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ ተሳትፏቸው በመምረጥና በውሳኔ ሕዝብ (ሬፈረንደም) በመሳተፍ ብቻ የተገደበ ይሆናል። ይህም በመሆኑ የማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት/ቡድን ወይም ስብስብ አባል ሊሆኑ አይችሉም። በፖለቲካ ለመሳተፍም ይሁን የድርጅት አባል ለመሆን የሚፈልጉ የመከላከያና የፖሊስ አባላት በቅድሚያ ከሰራዊቱ መሰናበት ይኖርባቸዋል። የመከላከያና የፖሊስ ሰራዊት አባላት ደህንነት መጠበቅ፣ የጡረታ መብታቸውን ማስከበር፣ በግዳጅ ላይ ለተሰዉ አባላት ቤተሰቦች ተገቢውን እርዳታና እንክብካቤ ማድረግ ከመከላከያ ፖሊሲያችን ውስጥ ሁነኛውን ቦታ ይይዛል። ከዚህም በቀር፣ በሀገራችን በኢትዮጵያ የውጭ ሀገር የጦር ሰፈሮች መቋቋምን አጥብቆ የተከለከለ መሆኑና የጦርና የወታደራዊ ጥገኝነት እንዳይፈጠር ማድረግ የመከላከያ ፖሊሲያችን መሰረት ነው።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ መከላከያ ሰራዊት፣ የተመሰረተበትን አላማና ግዴታ ለመፈጸምም ሆነ፣ ተልዕኮውን በብቃት ለመወጣት የሚያስችለውን ሥልጠና፣ ትጥቅ፣ አደረጃጀትና ስንቅ ለሟሟላት የሚያስፈልጉት የትምህርት ተቋማት ሁሉ ተሟልተው ሊቋቋሙለት ይገባል። ልዩ ልዩ የሙያ ዘርፎችን ለሟሟላት ብቻ ሳይሆን፣ መሰረታዊ የሆነውን ወታደራዊ ሳይንስን ለማስተማር የሚያስችሉ ከፍተኛ የትምርት ተቋማትና ወታደራዊ አካዳሚዎች፣ የአየር፣ የየብስና የባህር መከላከያ ከወቅቱ የቴክኖሎጂ ጋር የተቀናጁ ዘመናዊ የጦር መሳሪያዎች ሁሉ ተሟልተው መገኘታቸው አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ግዴታም ጭምር መሆኑን ለሀገሩ ነጻነት ዋስትና እንዲኖረው የሚፈልግ ዜጋ ሁሉ ሊገነዘበው ይገባል። የሀገሪቱ ብሔራዊ ሃብትና የኤኮኖሚ አቅም በፈቀዱት መጠን፣ ሀገራችን ለራሷ መከላከያ የሚያስፈልጓትን የጦር መሳሪያዎችን፣ የትጥቅና የስንቅ፣ የመጓጓዣና የመገናኛ አገልግሎት የኤሌክትሮኒክስ ቴክኖሎጂ እቃዎችን የምታመርትባቸው ፋብሪካዎችና ተቋሞች እንዲኖራት ማድረግ፣ የመከላከያ ሰራዊቷን ብቃትና ዝግጁነት ያረጋግጥላታል ብለን እንመኛለን። ከአፍሪካ አህጉር በቆዳ ስፋቷ በሶስተኛ ደረጃ የተመደበችውና የሕዝቧም ቁጥር ከሰማኒያ ሚሊዮን በላይ የሆነች ሀገር፣ ከሁሉም በላይ ቅድሚያ ከምትሰጣቸው ሀገራዊ ፖሊሲዎች መካከል፣ የመከላከያ ኃይሏን ማጠንከር ለመሆኑ የሀገሩን ሕልውና መጠበቅ የሚመኝ ዜጋ ሁሉ ይስማማበታል።

ከሰሃራ በረሃ በታች ካሉት የአፍሪካ ሀገሮች ውስጥ በትጥቅም ሆነ በብዛት፣ በሀገር ወዳድነትም ይሁን፣ በጀግንነት ተወዳዳሪ ያልነበረውን የሀገሪቱን የመከላከያ ሰራዊት፣ የውጊያ ብቃቱንና ወታደራዊ ሥነ ሥርአት(ዲሲፒሊን) ሊፈታተኑት ካስቻሉት ምክንያቶች አንዱ፣ የፖለቲካ ካድሬዎች በሰራዊቱ ውስጥ ተሰግስገው ያመጡት ጉዳትና ጥቃት ነው። የዚህ ውጤት ደግሞ የሀገሪቱን አንድነት ያናጋው ብቻ ሳይሆን ዳር ድንበሯንም ጭምር አስደፍሮ ታሪኳን አዋርዶ ሕዝቧንም ያሳፈረና አንገት ያስደፋ ሆኗል። የእኛ እምነትና ራዕይ፣ የነገዋ ኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲም ሆነ የብሔር ድርጅት ቁጥጥር የፀዳና በማንም የፖለቲካ ካድሬ ተውሳክ የማይበክለው ሙያተኛ ተዋጊ ኃይል መገንባት ነው። በዚህ ለሀገራችን ነጻነትና አንድነት ባለን አቋም ምክንያት፣ በጠባብ ብሔረኞች ዘንድ „አባይ ኢትዮጵያ“ የሚል ምጸት ሲነገርብን ቆይቷል። ታላቅ ኢትዮጵያ መባላችን የሚያኮራንና የምንደሰትበትም ስለነበረ ዛሬ የወያኔዎችን ምጸት የምንጠቅሰው፣ በአባይ ኢትዮጵያዊነታችን፣ ሀገራችንን ኢትዮጵያን ከጥፋት አድነን የነገዪቱን ታላቂቷን ኢትዮጵያ ለመገንባት ነው። አባይ ኢትዮጵያን አስከብረንና አኩርተን በነጻነቷና በአንድነቷ የታፈረች፣ የተከበረች ሀገር መሆኗን ማየት የአላማችን አልፋና ኦሜጋ ነው። የጠባብ ብሔረተኞችን የምጸት አነጋገር እንደ ፍሬ ከርሲስኪ የምንቆጥረውም ለዚሁ ነው።

አስተማማኝና የማይበገር የሀገር መከላከያ ሠራዊት ለመገንባት ከሚያስፈልጉት መሰረታዊ ጉዳዮች መካከል፣ ለዚህ አገልግሎት አይነተኛ የሆኑትን የትምህርት ተቋማትን ማቋቋም ነው። ለሀያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የሚስማማ መከላከያ ኃይል መገንባት ካስፈለገ ለዚሁ ዘመን የሚሆኑ ወታደራዊ ትምህርት ቤቶችና የጦር መኮንኖችን የሚያሰለጥኑ ከፍተኛ አካዳሚዎች መመስረት የሚያከራክር አይሆንም። ቀደም ሲል ተቋቁመው የነበሩት ወታደራዊ ተቋማትና አካዳሚዎች ከመፍረሳቸው በላይ ኬኒኒህ ወታደራዊ ማሰልጠና ተቋማትና አካዳሚዎች ሰልጥነው የተመረቁት ወታደራዊ መኮንኖችና ምሁራን በብዛት

እንዲጠፉ ተደርገዋል። የአንድን ሀገር የሰለጠነ ወታደራዊ ኃይልና መኮንኖችንም ጭምር ማጥፋት የሚጠበቀው ከቅኝ ገዢዎች እንጂ ኢትዮጵያዊ ነኝ ከሚል ቡድን ባልሆነ ነበር።

በሶስተኛው የአለም ሀገሮች ተወዳዳሪ ያልነበረው የሐረር ጦር አካዳሚ ፈራርሶ የጉፋያ ማስጫ መሆኑን ማየት፡ የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን የሚያስቆጭም ሆኗል። ለእጩ መኮንኖች ማሰልጠኛ ተብለው የተደራጁት፡ የሳይንስ ላቦራቶሪ መሳሪያዎች፡ የልብስ ማጠቢያ (ላውንደሪ) ማሽኖች ተነቃቅለው ወደሚሄዱበት ተወስደዋል። የአካዳሚው መጻህፍት ቤት ተመዝብሯል። የአካዳሚው እጩ መኮንኖች እንዲሰለጥኑበት ውድ ዋጋ ተከፍሎባቸው ከውጭ ሀገር የተገዙ ምርጥ ምርጥ ፈረሶች በሀራጅ እየተሸጡ ደብዛቸው ጠፍቷል። ዝነኛው የኢትዮጵያ አየር ኃይልም ከዚህ አሳዛኝ እድል ሊያመልጥ አልቻለም። ስመ ጥር የነበረው የፖሊስ አካዳሚም ከዚህ የብሔራዊ ጥፋት መአት አላመለጠም። በአሁኑ ወቅት ስለ ባህር ኃይል አካዳሚ ማውሳት፡ ልክ በምድረ በዳ እንደመጮህ ስለሚቆጠር ጊዜ ይፍታው ብሎ ከማለፍ የተሻለ አስተያየት መኖሩን እንጠራጠራለን። ምንም ምን ተባለ፡ የኢትዮጵያን ማንነት ለማጥፋትና የባዕዳንን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲል ከጉያ ከበቀለ ጠላት በጎ ነገር ስለማይጠበቅ፡ ያሁኑን ሁኔታ ለመለወጥ ካስፈለገ፡ ይህን የዘረኛ ሥርአት አራማጅ ቡድን ከማስወገድ የበለጠ አማዳፊ ተግባር ሊኖር አይችልም።

በኢትዮጵያ ሕዝብ እምነትም ይሁን በእኛም አመለካከት፡ በሀገሪቱ አንጡራ ሀብትና በኢትዮጵያ ሕዝብ ሥም የተቋቋመ የመከላከያ ሰራዊት፡ በመሰረቱ ሊሆን የሚችለው የሀገሪቱ የመከላከያ ሰራዊት ነው። በአጠራርም ይሁን በአተረጓጎም፡ በአገልግሎትም ይሁን በታማኝነት የሙያ ግዴታውን የሚወጣው ለሀገር እንጂ ለማንም የብሔር ድርጅትም ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አይደለም። የዚህም ቀጥተኛ አስተጋብዖ ተጠያቂነቱና ኃላፊነቱ፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ እንደሆነ ያረጋግጥለታል። ይህም በበኩሉ የኢትዮጵያ ብሔራዊ መከላከያ ኃይል እንጂ፡ በየጊዜው ለሚፈራረቁ አምባገነን ሥርአቶች መሳሪያ እንዳይሆን ያግደዋል። ምንም እንኳን ደርግ የራሱን የጭካኔ አገዛዝ ለማራመድ ሲል በአብዮት ሥም የነበልባል ቡድን አቋቁሞ ብሔራዊ ወንጀል ሲፈጽም እንደነበር ሁሉ፡ ዛሬም ወያኔ ሕዝብ የሚጨፈጭፍበት የአግአዚ ጦር መስርቶ በሰላማዊ ሕዝብ ላይ የሚያካሂደውን የግድያ ወንጀል መፈጸሙ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የተሸሸገ ባይሆንም፡ ሌላው ተዋጊ ሰራዊት ግን የወገኑን ደም በጭካኔ እንደማያፈስ ጠንቅቆ ሊገነዘብ ይገባዋል። የሀገሪቱን ዳር ድንበር ለመጠበቅ ሲል ደሙን እያፈሰሰ አጥንቱን እየከሰከሰ ከውጭ ጠላት ጋር መፋለም የሚገባው ተዋጊ ሰራዊት፡ ከሀገሩና ከሕዝቡ ጋር በገባው ቃል ኪዳን መሰረት፡ የመሳሪያውን አፈሙዝ ወደማን እንደሚያዞር በሚገባ ማወቅ አለበት። የመከላከያ ሰራዊት፡ የሀገሩን ሕገ መንግሥት ብቻ ሳይሆን፡ የአለም አቀፍ ደንቦችንና ሕግጋትን መረዳት የሚያስችለውን በቂ ትምህርት እንዲያገኝ ማድረግ ይሆናል። የኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት ሀያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የሚጠይቀውን ሁለንተናዊ የወታደራዊ ሳይንስ እውቀትና ጥበብ ማግኘት እንዳለበት ከልብ የምናምንበት ታላቅ ቁም ነገር ነው። ቅስ! ጊዜ ለኩሉ ወይም ለሁሉም ጊዜ አለው እንዲሉ ግን የዛሬ ዋናውና ቀዳሚ ግዳጃችን የወያኔን አገዛዝ ገርስሦ ማስወገድ ነው። ይህም ግዳጅ የወያኔን የአፈና ኃይልና ጦር በእይታ አስገብተን ማቸነፍም ማሸፈትም መቻልን የግድ ይላል።

ከትዝብት አድማስ ቁ 85
ጥር 26 ቀን 2002 ዓ.ም.

## *የኢሕአፓ የኤኮኖሚ ፖሊሲ*

*ሀገራችን ኢትዮጵያ በድህነቷ ከአለም ሀገሮች መካከል የመጨረሻውን እርከን የያዘች መሆኗ ዘወትር ተደጋግሞ የሚገለጽ ስለሆነ ያንኑ መዘርዘር አስፈልጎ ሆኖ አናገኘውም። ለዚህም ነው ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ብሔራዊ ኤኮኖሚያችንን እንደምንም ብለን መገንባት ይኖርብናል የምንለው። ለድህነታችን ምክንያቶች የሆኑትን መሰረታዊ ችግሮቻችንን በሂደት ለመቅረፍ፡ ብሔራዊ ብልጽግናን ኢላማ ያደረገ የሕዝቡን ጥቅም ያካተተና ቅድሚያ የሰጠ፡ በገበያ ኤኮኖሚ መርኅ ላይ የተመሰረተ ብሔራዊ ኤኮኖሚ መገንባት የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል አይነተኛ ይኖረዋል። ሰማኒያ አምስት በመቶ የሀገራችን ሕዝብ ኑሮ የተመሰረተው በግብርና ላይ በመሆኑ፡ በዋናነት የመሬቱን ይዞታ መለወጥ፡ መሬት ለአራሹ በባለቤትነት በሕግ እንዲረጋገጥለት ማድረግ ወሳኝ ነው። የሀገራችን አርሶ አደሮች በሚያርሱት መረት የባለቤትነት ይዞታ በሕግ የተረጋገጠላቸው ብቻ ሳይሆን፡ የመሸጥ የመለወጥ፡ የማውረስ፡ በዋስትና(በወለድ አግድ) የማስያዝ መብታቸው የማይደፈርና የማይገሰስ ሊሆን ይገባል። መሬት አልባ የሆኑ አርሶ አደሮች፡ በኅብረተሰቡ ስምምነትና ድጋፍ የሚታረስ መሬት በንብረትነት ማግኘት የዜግነት መብታቸው ይሆናል። ዘመናዊ እርሻዎችን ለማቋቋም ለሚሹና ለሚችሉ በግብርና ለሚተዳደሩ ዜጎች መንግሥት የረዥም ጊዜ ውል (በኮንሴሽን) ይሰጣል። የሚሰጠውም መሬት መጠኑም ሆነ የይዞታው (የኮንሴሽኑ) ሁኔታ በህግ ይወሰናል። መንግሥት የአርሶ አደሩ የኑሮ ደረጃ ከፍ እንዲልና ምርቱም እንዲዳብር ለአርሶ አደሮች አስፈላጊውን እርዳታና አገልግሎት ለምሳሌ ምርጥ ዘሮች፡ የሰብል ተባይ መከላከያ፡ የግብርና መገልገያ መሳሪያዎችንና የመሳሰሉትን ከቀረጥ ነጻ ሆነው የሚቀርቡበትን ሁኔታዎች ሊያመቻች ግዴታ አለበት። አብዛኛው የሀገራችን ነዋሪ፡ ሕይወቱ የተመሰረተው በእርሻ ተግባር እንደመሆኑ፡ ለገጠሩ ዜጋ ከኑሮው ጋር የተያያዙ አገልግሎት የሚሰጡ መጋቢ መንገዶች፡ ትምህርት ቤቶች፡ ክሊኒኮች፡ የዕደ ጥበብ ማሰልጠኛ ማዕከሎች፡ የመስኖ ግድቦች፡ ቦዮች፡ የጉድጓድ ውሃ በአቅራቢያ የሚያገኙበትን ዘዴ ሁሉ ማመቻቸት የመንግሥት የሥራ ድርሻ ሊሆን ይገባል።*

*ዘመናዊ የርሻ ዘዴን ለማስተዋወቅ፡ የእንስሳትን እርባታ፡ የአትክልትና አዝርዕት፡ ዛፎችንና ደኖች፡ የቤት እንስሳትን እርባታም ሆነ የዱር አራዊትን ጥበቃና ደህንነት ለማረጋገጥ ያልተቋረጠ ጥረት ማድረግ ከጠቅላላው የኤኮኖሚ ፖሊሲ ተለይቶ የሚታይ አይደለም። ወንዞችና ጅረቶች ለእርሻና ኢንዱስትሪ ጣምራ ግላጋሎት የሚሰጡበትን እቅድ ማውጣት የቅድሚያ ግዴታው፡ የሀገሪቱ መንግሥት መሆኑ ቢታወቅም፡ በዚህ ከፍተኛ የኤኮኖሚ ግንባታ ሂደት፡ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱበት ሁኔታ ሊመቻችላቸው ይገባል። የሀገራችን አዕዋፍ ብሔራዊ ሀብታችን ስለሆኑ፡ ተንከባካቢ በማጣት ለዘመናት በመሰደድ፡ ዘራቸው በመጥፋት ላይ መሆኑ ታውቆ አስፈላጊው መከላከል ሊደረግላቸው ይገባል። በልዩ ልዩ አቅጣጫ ከሀገር የሚሰደዱት ታላላቅ ወንዞቻችን በዘመናት እየጠራረጉ የሚወስዱት ለም መሬት፡ ሀገራችንን ወደ ምድረ በዳ እየለወጣት መሄዱን ያልተገነዘበና መፍትሄ ለማግኘት የሚቻልበትን መንገድ የማይሻ መንግሥትና ማንኛውም ዜጋ፡ ስለሀገሩ ኤኮኖሚ እድገት ይቆረቆራል ብሎ ማሰብ*

ይቸግራል። ታላልቅ ወንዞቻችን የኤሌክትሪክ መብራት ማመንጫ ኃይል መሆናቸው ቀርቶ፣ ለም አፈራችን እየዘረፉ ለባዕዳን መጠቀሚያ እንዲያደርጉ መፍቀድ የዛሬውን ነዋሪ ብቻ ሳይሆን፣ የመጭውን ትውልድ ሃብት ማዘረፍ ይሆናል።

በእርሻ ላይ የተመሰረተ ኢንዱስትሪ(አግሮ-ኢንዱስትሪ) ማስፋፋት ተመጣጣኝ የሆነ የእድገት እርምጃ ማምጣት የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎቱና ምኞቱ መሆኑ የታወቀ ነው። ያልተነካው የሀገራችን ድልብ የተፈጥሮ ሀብት፣ የከርሰ-ምድር ማዕድናትና ሌሎችም ቁልፍ ብሔራዊ ሀብት በሙሉ ለሕዝብ ጥቅም የሚውሉበትን ሁሉ ማድረግ ከድኅነት እንድንላቀቅ፣ የባንክ የፋይናንስና የመድህን(ኢንሹራንስ)መስፋፋት፣ በሀገራችን የኤኮኖሚ ፖሊሲ ሕግና ሥርአት እንዲከናወን ማድረግ፣ ማንም ድርጅት ወይም የመንግሥት ባለሥልጣን ያላግባብ እንዳይጠቀምበት ማገድ ወሳኝ ነው። በነጻ ገበያ ላይ የተመሰረተ ኤኮኖሚ ፖሊሲ የሕዝቡን ሙሉ ተሳትፎ የሚያስተናግድ እስከሆነ ድረስ፣ ከድኅነታችን ለመላቀቅ በሚደረገው ጥረት ተገቢውን ሚና እንደሚጫወት እንረዳለን። ሰርቶ አደሩን ሕዝብ ግን ለጭፍን ብዝበዛ አሳልፎ የሚሰጥ ጨካኝ ሰው በላ ሥርአት እንዳይሰፍን ኢሕአፓ አጥብቆ ይከላከላል።

የሰለጠነውን የሰው ኃይል ጉልበት ከገበሬውና ከሰራተኛው ጋር እንዲሁም ከሀገሪቱ የተፈጥሮ ሀብት ጋር አስተባብሮና አቀነባብሮ የእድገት ጎዳና ለመቀየስ፣ በሕግ የተመሰረተ ነጻ የኤኮኖሚ ፖሊሲ መዘርጋት የግድ ነው። ይህ ፖሊሲ ሀገራችንን የአለም ተመጽዋች እንዳትሆን ከማድረጉም በላይ በራሳችን እንድንተማመን ያደርገናል። በተሻለ መጠን ተመሳሳይ የእድገት እርምጃ የሚያስገኝልንን የብሔራዊ ኤኮኖሚ ፖሊሲ መዘርጋት፣ ከድኅነታችን ለመላቀቅ የሚረዳን መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ለአንድነታችን ጥንካሬም በእጅጉ ይጠቅማል። በአለም ውስጥ እጅግ ድሃ ተብለው ከተፈረጁት 12 ሀገሮች መካከል ኢትዮጵያ ሀገራችን አንዷ መሆኗን መረዳታችን ዘወትር የሚያሳዝነንና የሚያስቆጨን ጉዳይ ነው። ከሃያ አምስት አመት በፊት ከተከሰተው ከዚያ አሰቃቂ ረሃብ በኋላ፣ ዛሬ እንደገና ከአስራ ሶስት ሚሊዮን በላይ የሚሆን ሕዝብ ለሌላ ረሃብ በመዳረጉ፣ የአለም አቀፉን አስቸኳይ እርዳታ ለማግኘት እጁን ዘርግቷል። የሕዝቡ ቁጥር በፍጥነት እያደገ መሄድና የምግብ አቅርቦቱ እጅግ ተመጣጣኝ ባለመሆኑ ለረሀብተኝነታችን የበኩሉን አስተዋጽዖ አድርጓል።

ከመቶ ሰባ አምስት የሆነው የገጠር ነዋሪ ሕዝብ ንፁህ የመጠጥ ውሃ አያገኝም። ስድስት በመቶ የሚሆኑ የገጠሪቱ ኢትዮጵያ ሴቶች፣ የመጠጥ ውሃ ቀድቶ በእንስራ ተሸክሞ ለመምጣት በቀን ከስድስት እስከ ዘጠኝ ኪሎሜትር መነገድ በእግር ለመሄድ ይገደዳሉ። የጤና ጉዳይ ከተነሳም ደግሞ ያለው ሁኔታ አሰቃቂ ነው። አምራቹ ኃይል በወባና በዘመናዊ በሽታ መያዙ እድገት ላይም አሉታዊ ተፅዕኖ አለው። የበርካታ ታላላቅ ወንዞችና ጅረቶች ባለቤት የሆነች ሀገራችን እስከዛሬ ድረስ ለእርሻ መሬቷ የምትጠቀምበት የመስኖ ውሃ ከመቶ አንድ ነጥብ ስድስቱን ብቻ ነው። ድኅነት ብሔራዊ መለያዋ የሆነችው ሀገር፣ በየአመቱ ከአስራ ሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ የውጭ እርዳታ ማግኘቷ ቢመዘገብም፣ ገንዘቡ ወደ ወያኔ ኪስ ስለሚገባ ድህነቷ ሊቀረፍላት አልቻለም። ከዛሬ አስር አመት በፊት በቤኒን ዋና ከተማ ኮቶኑ የተደረገው ስምምነት፣ የአውሮፓ ኮሚሽን ለኢትዮጵያ የሚያደርገው እርዳታ ከሰብአዊ መብት መከበር ጋር መያያዝ አለበት የሚል ውሳኔ ማስተላለፉ ቢታወቅም፤ ዛሬ የሀገሪቱ ዜጎች በግፍ እየታሰሩ

እየተገደሉና በብዛትም በመሰደድ ላይ ናቸው። በኢትዮጵያ ስም የሚጎርፈውም የውጭ እርዳታ የወያኔ ባለሥልጣናትና ወገኖቻቸውን ማበለፀጊያ ሆኖ ቀርቷል።

አግላይ የሆነ የፖለቲካ ሥርአትና አድሏዊ የሆነ የኤኮኖሚ ፖሊሲ፤ የሀገሪቱን የጋራ ሀብት እየነጠቀ ለሥርአቱ አቀንቃኞች መንደላቀቂያና መክበሪያ አድርጎታል። ፀረ ኢትዮጵያ አቋማቸውና የሕዝብ ጥላቻቸው የቱን ያህል ሥር የሰደደ መሆኑን ለመግለጽ ይሆናል፤ ወያኔዎቹ የሀገሪቱን የድንበር ግዛቶችና ለም የርሻ መሬቶች ለባዕዳን በመቸብቸብ ላይ የሚገኙት። የኢትዮጵያ የቅላላ የመሬት ስፋት 1 127 200 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ሲሆን፤ ዛሬ 64 000 ስኩዌር ኪሎ ሜትር (ከመቶ 6) የሚሆነው መሬት ለሱዳን ተሰጥቷል። ይህ ለሱዳን የተሰጠው መሬት ከ200 አመታት በላይ የኢትዮጵያ ለመሆኑ በአለም አቀፍ ደረጃ የተረጋገጠ ነው። ይህ በጠረፍ አካባቢ የተወሰደው የኢትዮጵያ መሬት፤ ርዝመቱ 1600 ስኩዌር ኪሎሜትር ሲሆን፤ ስፋቱ ደግሞ 40 ስኩወር ኪሎሜትር ነው። የጂቡቲን የመሬት ስፋት በሶሥት እጥፍ ይበልጣል። ይህ ወያኔ ለሱዳን የሸለገው መሬት በስፋቱና በለምነቱ ብቻ ሳይሆን፤ በውስጡ በሚኖሩ አራዊትና እንስሳት፤ አዝርዕትና እፅዋት ጭምር ተወዳዳሪ የማይገኝለት ነው።

በእኛ እምነት፡ ማንናውም የፖለቲካ ሥርአትም ይሁን የኤኮኖሚ ፖሊሲ የአንድን ሀገር የልማት እርምጃ ሊያፋጥን የሚችለው፤ በቅድሚያ በሀገሪቱ ዴሞክራሲያዊ ሥርአት እውን ሲሆንና ቀጥሎም የኤኮኖሚው መሰረትና ይዘት፤ የሀገርን ብሔራዊ ጥቅም ያስቀደመ ሆኖ ሲገኝ ነው። የሕዝብን መሰረታዊ ነጻነትና መብት ማስከበርና የኤኮኖሚ እድገት ተነጣጥለው የሚታዩ አይደለም። አንዱ ከሌላው ጋር ተደጋጋፊ እንጂ ተፃራሪ አይሆንም። በነጻ የመንቀሳቀስ መብት ከሌለ፤ በራስ አነሳሽነትና እፍላቂነትን መሰረት ያደረገ የልማት እንቅስቃሴ ማድረግ ከቶ የሚቻል አይሆንም። በዘር ላይ የተመሰረተ የክልል አገዛዝ አውቅሮ በጋራ ሀብት ላይ የተመሰረተ የጋራ እድገትና ብልፅግና ሊመጣ አይችልም። ከሌሎቹ የሀገሪቱ ክፍላተ ሀገር በሚዘረፍ ሀብት የአንድን አካባቢ ለማበልፀግ የተዘረጋ የልማት እቅድ፤ እድገትን ቀርቶ ሰላምንና መረጋጋትን አያስገኝም። የእኛ የኤኮኖሚ ፖሊሲ ራዕዩ ሰፊና በሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የኑሮ እድገት ላይ ያተኮረ ነው። የሀገሪቱ ብሔራዊ ሀብት የጠቅላላው የሀገሪቱ ዜጎች ሀብት መሆኑን ስለምናምን፤ ጠቃሚነቱና አገልግሎቱ ያለምንም አድሎዖ የሁሉም ዜጋ ነው። የዚህ ረዥም ራዕይ የኤኮኖሚ ፖሊሲ ዋስትናው፡ የሕግ የበላይነት፡ የሰብአዊ መብቶች ያለምንም ገደብ መስፈን፡ የሀገር ነጻነትና ሉአላዊነት መከበር ነው።

ዛሬ ሀገራችን ኢትዮጵያ የባዕዳን ርካሽ ሸቀጥ ማራገፊያ በመሆኗ፤ መለስተኛ አቅም ያላቸው ነጋዴዎች ተጠቅተዋል። ብሔራዊ ኤኮኖሚን የሚገነቡ ነጋዴዎች እንቅስቃሴና እድል ተዳክሟል። አርሶ አደሩ የመሬቱና የላቡ ተጠቃሚ እንዳይሆን፡ በስግብግቦቹ የወያኔ ቡድኖች ታግዷል። ባዕዳን፡ በሀገራችን የውስጥና የውጭ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት ያሻቸውን ለማድረግ ኃይልና ነፃነት አግኝተዋል። ይህም ሀገሪቱን የእጅ አዙር ቅኝ ግዛት አድርጓታል ለማለት ያስችላል። የሀገራችንን የፖለቲካ ችግር፡ የኤኮኖሚ ድቀት፡ የማህበራዊ ቀውስ፡ የሕዝቡንም ሁለንተናዊ መከራና እሮሮ ለማስወገድ በግድ ይህ ዘረኛ ሥርአት መወገድ አለበት።

## የወያኔ የጅምላ የአባላት ምልመላ
## የመጨረሻው የሀገር ማጥፋት ተልዕኮው
## ማስፈጸሚያ መሆኑን ማጤን ይገባል።

ከአምሮ በለጠ አዲስ አበባ

የ 2002 ዓ.ም የምርጫ ተብዬው ቀዜማ ላይ የወያኔ በግዳጅ ዜጎችን አባል የማድረግ ድርጅታዊ ድራማ ለምን የሚለው ጥያቄ ከትንሽ እስከ ትልቅ ከገጠር እስከ ከተማ፣ የገበሬው የላብ አደሩ፣ የተማረውም ያልተማረውም፣ የተማሪው የአስተማሪው፣ የሀኪሙ የመሀንዲሱ፣ የነጋዴው የደላላው፣ የዳኛው የጠበቃው፣ የሴቶች የወጣቶች፣ በአጠቃላይ የህዝቡ መነጋገሪያ ከሆነ ሰነበተ። ወያኔ በደርግ አምባገነን ወንበር ላይ ከተፈናጠጠበት የዛሬ አሥራ ስምንት አመት ጀምሮ ህዝብ እንዳማረረው፡ እንደጠላው ሊጥለው የታገለውና እየታገለውና እያንገዳገደው እንዳለ የታወቀ ነው። እንደማንኛውም የአፍሪካ አምባገነኖች የወያኔ ህልውና የተመሠረተው በጠር መሣሪያ ኃይል ነው። የጦር ሠራዊቱን፣ የፖሊስ ኃይሉን፣ ደህንነቱን፣ የፍትህ ሥርአቱን፣ እንዲሁም የሀገር ሀብትን በፈላጭ ቆራጭ ቁጥጥሩ ሥር በማድረግ ብቻ ነው። የሀገርን ሀብት አሿጠ የሥልጣን ዘመኑን ለማራዘሚያ መጠቀሙ የኢትዮጵያ ህዝብን በድህነት አረንቋ እንዲተበተብ አድርጎታል። በዚህም ተደጋግሞ እንደተነገረውና እንደሚታወቀው አገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ ለሰፊው ህዝብ ገሀነም ስትሆን ለጥቂት የትግራይ ብሄረሰብ ተወላጆችና በሥራቸው ለተኮለኮሉ ሆዳቸውን ከሀገራቸው ጥቅምና ከህዝባቸው ነፃነት ላስቀደሙ ምድር ገነት መሆኗን በአንክሮ ማየቱ የግድ ይሆናል። የኢትዮጵያ ህዝብ የድህነት ደረጃን መግለጽ ከሚቻለው በታች አሽቆልቁሎ ከእጅ ወደ አፍ ከእለት ጉርስ ኑሮው በባሰ ሁኔታ ለጠም አዳሪነት ዳርጎታል። የወያኔዎች የምጸት ፕሮፓጋንዳ እነሱ በገንዘብ ክምችት አድገውና በሀብት ብዛት ተሰፋፍተው በጠኔ እየረገፈ ያለውን ህዝብ አድጓል እያሉ ነጋ ጠባ በማያልቅባቸው የቁጥር ቁማር ንዝንዝ አይሉት ማላዘን እንደቀጠሉ ነው። የህዝቡ መደኽየትን የዴሞክራሲ ኃይሉ በፖለቲካ ልምሻ እንዲሽመደመድ አድርጎታል። የወያኔ ውስጥ አዋቂዎች እንደሚነግሩን ከሆነ የህዝቡን እየደኸየ መሄድ ወያኔ የሥልጣን ዘመኑን ለማራዘም እየተጠቀመበት ነው። ደሀ የዛሬ ባዶ ሆዱን ለመሙላት ይጥራል፡ ይግራል፡ ይታገላል እንጂ የነገ የፖለቲካ ለውጥን ሊያስብ ቀርቶ የማሰቢያ ጊዜም አይኖረውምና ድህነትን እናጠፋለን አፍአዊ መርህ በማድረግ በተግባር ግን የህዝብንና የመንግስትን ሀብት እየመዘበሩና እየዘረፉ ድህነትን ማስፈን፡ ማጠናከር የወያኔ መርህ የማእዘን ድንጋይ ነው። ከዚህ በተጨማሪም ወያኔዎች ከድህነት ማምለጫው መንገድ አንድ ብቻ እንደሆነ መስበክ ከጀመሩ አመታት ተቆጠሩ። በአለፈው አመት በ2001 ዓ.ም ሀኔው እጅግ በባሰና ዐይን ባወጣ መልኩ ነጋዴዎችን፣ አርሶ አደሮችን፣ አስተማሪዎችን፣ ሀንፃ ተቋራጮችን፣ ዳኞችን፣ ጠበቆችን፣ የፋብሪካና የኢንዱስትሪ ባለቤቶችን፣ ሀኪሞችን፣ ጤና ረዳቶችን፣ ሥራ አጦችን፣ ወጣቶችን፣ ሴቶችን፣ አረጋውያንን፣ ፖሊሶችን፣ ወታደሮችን፣ መሀንዲሶችን የእትዮጵያን ህዝብ በአጠቃላይ የወያኔ በግድ አባል እንዲሆኑ ማድረግና ኣባል ያልሆኑት ላይ የተለያዩ ተጽእኖዎችን በማሳደር ህዝቡን በማሸበር ለመግዛት ማቀዱን ይፋ አድርጎታል።

ይህን የወያኔን የአባልነት ጥያቄ አለመቀበል እንደ ፖለቲካ ባላንጣነት የሚያስፈርጅ ብቻ ሳይሆን እንደ ወንጀለኛም እንደሚያስቆጥር የወያኔ ካድሬዎች በይፋ በየስብሰባው አስጠንቅቀዋል። ይህን የግዳጅ የአባልነት ጥያቄ አለመቀበል የዜግነት መብቶችን ያስገፍፋል። አጠቃላይ የሥራ ዋስትናን ያሳጣል፤ በፈጠራ ወንጀል ዘብጣያ ያስወርዳል።

የወያኔ አባልነትን ያልተቀበሉ የመንግስት ሠራተኞች የደረጃ እድገት ይከለከላሉ፣ ከደሞዝና ከደረጃ ዝቅ እንዲሉ ይደረጋሉ፣ ከሥራ ይባረራሉ። በዜግነት ማግኘት የሙያ ሥልጠናና የትምህርት ዕድልንና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ይነፈጋሉ ይከለከላሉ። በመስከረም 2002 ዓ.ም. በተለያዩ የሚንስትር መስሪያ ቤቶችና እንዲሁም በሌሎች የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ ይሰሩ የነበሩ ሠራተኞች የአባልነት ጥያቄን ባለመቀበላቸው ጥቂት ሠራተኞች ከእድገት ዝቅ እንዲሉ ሲደረግ በርካቶች ግን ከሥራ ተባረዋል። ወጣቶች የወያኔን የግዳጅ አባልነት ጥያቄ ያልተቀበሉ ወጣቶች ከተመረቁ በኋላ የሥራ ማስታወቂያ አይቶ ለመመዝገብ የወያኔ የድጋፍ ደብዳቤ በጣም አስፈላጊ በመሆኑ በርካታ ተማሪዎች በአገራቸው ሠርቶ የመኖር መብታቸውን ተገፈዋል።

የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ሳይቀሩ በግዳጅ የአባልነት ፎርም እንዲሞሉ ተደርጓል። ከ18 አመት በታች የሆኑ ህፃናት በግዳጅ የፖለቲካ ጫና መፍጠር ህፃናቱን መሣርያ አስታጥቆ ወደ ጦር ሜዳ ከመላክ ተነጥሎ አይታይም።

ይህ የወያኔ የግፍ የግዳጅ ምልመላ ከ 2002 ዓ.ም. ምርጫ ጋር የተገናኘ ቅድመ ዝግጅት አካል መሆኑ ይታወቃል። የ 1997 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ህዝብ ወያኔን አንቅሮ የተፋበት ውጤትና የወቅቱ ሀገራዊና አለም አቀፋዊ ተጨባጭ ሁኔታ ወያኔን አሸብሮታል። የወያኔ መሸበር ምክንያቱ እሸነፋለሁ የሚል ስጋት ሳይሆን ህዝቡ ወያኔ ባዘጋጀውና አማራጭ በሌለበት ለሚደረግ የምርጫ ቧልት ድምጽ ላለመስጠት ከቤቱ ላለመውጣት ያድማል የሚል ጥርጣሬ አለውና ነው። ይህን ለመከላከል ከወዲሁ በግዳጅ ህዝቡን አባል በማድረግ የአባልነት ግዴታውን እንዲወጣ ሽብርንና ማስፈራራትን በመጠቀም ምርጫ ተብየውን ድራማ ቀለሙን ለማድመቅ ህዝቡን ለመቀስቀሻነት ለመጠቀም ታስቧል። ይህ ካልሠራ በወታደሩና በፖሊሱ በማስፈራራትና የኃይል እርምጃም በመውሰድና እንዲሁም ወታደሩንና ፖሊሱን በምርጫ ጣቢያው በማዘዋወር እንደተለመደው ድምጽ እንዲሰጡ ማድረግ ሌላው ዘዴ ተብሎ የተያዘ ነው።

የገፍ የወያኔ አባልነት ምልመላ የተጧጧፈበት ሌላው ሰበብ ዘንድሮ የሚካሄደውን የምርጫ ቧልት ህዝቡ በአመጽ የሚቃወመው መሆኑ ይታወቃልና ከወዲሁ የመለየት ሥራ መደረጉ መሆኑ የታወቀ ነው። የአባልነት ጥያቄ ቀርቦላቸው ፈቃደኛ ያልሆኑ ዜጎችን በመኖሪያ ሰፈራቸው፣ በመሥሪያ ቤታቸው፣ በማዝወተሪያ ቦታቸው ክትትል እንዲደረግባቸው፣ ስልኮቻቸው እንዲጠለፉ እንደሚደረግ ማወቅ ተችሏል። የወያኔ አዲስ ምልምሎች አንዱ ሥራ ቤተ ሰቡን፣ ጓደኛን፣ የሥራ ባልደረባን፣ ጎረቤትን፣ የእድር እንዲሁም የማህበር አባላትን መሰለልና በየጊዜው ሪፖርት ማድረግ ነው። ከዚህ በተጨማሪም አባላት እርስ በእርስ እንዲሳለሉና በጠለፋ መሰመር የተቀላለፉ መሆናቸውን ከነባር የወያኔ አባላት የተገኙ መረጃዎች ያረጋግጣሉ።

ወያኔ ይህንን የገፍ ምልመላ ሥራን ከዋነኛ የገቢ ምንጮቹ አንዱ መሆኑን እንረዳለን። የወያኔ አባላት ከግዴታቸው አንዱ በየወሩ ከገቢያቸው 4 ከመቶ መዋጮ መክፈል ነው። በዚህ ወቅት ወያኔ ስድስት ሚሊዮን አባላት እንዳሉት በተለያዩ ጊዜያት የገለጸ ሲሆን በደምሳሳው በወር የሚሰበሰበውን ስናሴለው 400 ሚሊዮን ብር የሚሰበስብ መሆኑን እንረዳለን። ይህ ገንዘብ የወያኔ ቁንጮዎችን ሀብት ለማዳበር እንደሚውል መረዳት ይቻላል።

ወያኔ በግዳጅ አባላትን የማበርከት ዘመቻው የጥፋት ተልዕኮው የመጨረሻው ምዕራፍ መሆኑን የፖለቲካ ተንታኞች ይስማሙበታል። ይህ አሠራር ከቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ እንደተቀዳ የፖለቲካ ተንታኞች አስረግጠው ይገልጻሉ። በአሸዋ ላይ የተሠራ ቤት ዶፍ የቀላቀለ ዝናብ ዘንቦ ጎርፍ ሲጎርፍ ድርምስምሱ እንደሚወጣ ሁሉ የወያኔም በግዳጅ በአባላት ብዛት መግዘፍ የዛሬ ህዝባዊ ጉምጉምታ ወደ ህዝባዊ አመጽ መቀየሩ አይቀሬ ነውና ያኔ ወያኔም ይንኮታኮታል።

„ሰብአዊ መብት በተረገጠበት፣ መብትን የጠየቁ ዛብጥያ በወረዱበት፣ የሕዝብ ድምፅ መሰረቁን የተቃወሙ መፈጀት ብቻ ሳይሆን በሺዎች በየማጎሪያው ተጥለው እስካሁን በሚሰቃዩበት ሁኔታና አሁንም ዜጎች እየታፈሱ በመታሰር ላይ እያሉ በምርጫ አለምንም ቅድመ ሁኔታ እንሳተፋለን ብሎ መነሳትና ለአገዛዙም ማሳወቁ ምናልባትም የሚሰቃዩ ዜጎችን መርሳት ይሆናልና ሊታሰብበትና ሊቀየር የሚገባው አቋም ነው። ዳኛ ብርቱካንም፣ አበራሽ በርታም፣ የዴዴሳ፣ ዝዋይ በሸለቆና ሸዋ ሮቢት ወዘተ የፖለቲካ እስረኞች ሁሉ ይፈቱ የሚል ቅድመ ሁኔታ ማቅረብ ይገባል/ይጠበቃል። ለመብት ሲታገሉ የታሰሩትን ረስቶ ለመብት እንታገላለን ማለት ዘበት ነው።“

የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእኮ)
-- መስከረም 26 ቀን 2002 ዓ.ም.

## የካቲት 11 -- የተረገመ የርጉሞች ቀን

በወርሃ የካቲት ደግም ክፉም ታይቷል። በየካቲት 12 የፋሽስቱ ግራዚያኒ ጦር የአዲስ አበባን ሕዝብ ጨፍጭፏል። የካቲት 66 ደግሞ የአጼውን ኋላቀር ስርአት ሕዝብ የገረሰሰበት መታሰቢያ ነው። ወያኔ ደግሞ የካቲት 11ን የምስረታ ቀኔ ነው ብሎ ሲያከብረው ይህ ቀን የርጉሞች ቀን ነው እንድንል ያስገድደናል።

የወያኔ መሪዎች ነጋ ጠባ የሚዋሹ ናቸውና ስለ ምስረታቸውም ብዙ ውሸት አሰራጭተዋል። ሕዝብ በአንድነት ሲታገል እነሱ በጠባብ ብሔረተኛነት መደራጀታቸውና ወደ ናቅፋ ዘልቀውም በሻዕቢያ እርዳታ ድርጅታዊ ነፍስ መዝራታቸውን ያድበሰብሳሉ። ሻዕቢያ በወቅቱ የኢሕአፓ ጦር መስራቾችን በሚቆጣጠረው ምድር አሳልፎ ወደ ትግራይ ለመስደድ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት መሆናችንን በቅድሚያ እመኑ ይል ስለነበር አዎ እናምናለን ያሉትን ወያኔዎችን በቅድሚያ ወደ ትግራይ ማሳለፉ ሀቅ ነው። የወያኔ መሪዎች አንድነት ያለ ሁሉ ተንኮለኛና ትምክህተኛ የሸዋ አማራ ነው፣ ትግላችን ትግራይን ገንጥሎ ነጻ መንግሥት ማቋቋም ነው ብለውና ኢሕአፓና ኢዲኅን አባይ ኢትዮጵያ ትምክህተኛ በሚል ፈርጀው ከትግራይ ውጡልን ማለታቸውንና ሁለቱንም መውጋታቸው ደግሞ ከቶም ሊካድ የማይችል ሀቅ ነው። በትግራይ ነጻ አውጪነት በራሳቸው የተደራጁ ሌሎች ወረተኞችንም እንደራደር ብለው ጠርተው በተኙበት መግደላቸውም ዛሬ ሊዋሸን የሚችል ጉዳይ አይደለም። የወያኔ መሪዎች ከዚያድ ባሬ ጋር ተወዳጅተው አንድ ሶስተኛ የኢትዮጵያ መሬት የምዕራብ ሶማሊያ ግዛት ነው ብለው መፈረማቸው ፀሃይ የሞቀው እውነት ነው። የወያኔ መሪዎች ትግላችን ፀረ አማራ ነው ብለው በወይን ጋዜጣቸው አስፍረውና ወጣቶችን ለሻዕቢያ ጦርነት በጠመንጃ ልዋጭነት እየማገዱ ከባዕዳን የኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር ሁሉ መስራታቸው የሚታወቅም ነው። ኢትዮጵያ አረብ ራቢጣ/ሊግ ትገባለች እኔም ራሴ አረብ ነኝ ሲል ለሊቢያው ጋዳፊ የለፈፈው የዜናዊ ልጅ መሆኑም የሚረሳለት የለም።

የካቲት 11 ከነበር ወያኔ የተወለደው ባስጨነገፈው በነበር በዚህ የተረገመ ቀን የምንለው ነው። ወያኔ ይህን ቀን ሲያከብር የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን እንደ የካቲት 12 በሀዘን የሚያልፈው ነው። ወያኔ ፀረ ሕዝብ የሆነ ሀገርን የጎዳ ቡድን ነው። ይህን ቀን ላክብር ብሎ ርችት ሲተኩስም ዜጎችን ገድሏል። ይህን ርኩስ ልደቱን አከበርኩ ለማለት ብዙ ሚሊዮን የሀገራችንን ብር አጥፍቷል፣ እያተፋም ነው። ዛሬ የባጡን የቆጡን የሚቀባጥሩት እነ መለስ፣ ስብሃት፣ ስዩምና አባይ ታሪክ ብለውም በመፅሃፍ መልክ ሀሰታቸውን ሲጎነጉኑ እየታዩ ናቸው። ሲወለድ ፀረ ኢትዮጵያ ሲቆይም ያው ፀረ ሕዝብ ፀረ ኢትዮጵያ ዘረኛ ቡድን ሆኖ ወያኔ መቀጠሉ ግን ከቶም ሊቀይሩት ወይም ሊቀብሩት የሚችሉት ሃቅ አይደለምና እነሱ የካቲት 11 በአላችን ነው ሲሉ ሕዝብ ደግሞ ተምቾች ተውሳኮች የተፈለፈሉበት ቀን ነው በሚል ይገልፀዋል። ባልተወለዳችሁ በቀራችሁ ነው የህዝብ መልዕክት። የካቲት 12 ሀገራችንን የወረረ ፋሺስት ጣሊያን ወገኖችን ጨፈጨፈ። የካቲት 11 ኢትዮጵያን ገንጣይና አዋራጅ፣ ሕዝቦቿን ከፋፋይ ዘረኛ ቡድን ተወለድኩ አለ። በናቅፋ ተረግዞና ተወልዶ በደደቢት ያደገው ወያኔ በባ ዕዳን ድጋፍ አድጎ ለቤተ መንግሥት በቅቷል። ከገባበት ቤት ስናስወጣውና የያዘውን ሥልጣን በሀይል ስንነጥቀው ያንን ቀን የኢትዮጵያ ሕዝብ ድል ቀን ብሎ ያከብረዋል።

## *ምን ማድረግ አለብን?*

በአሁኑ ጊዜ የወያኔ አገዛዝ የሕዝብ ትኩረት በግንቦቱ የወያኔ ምርጫ ተብዬ ጉድ ላይ እንዲያተኩር ነው። ተስፋን እየመገበና አንዳንዶቹም ወያኔ በራሱ ምርጫ ሲሸነፍ የሚታያቸውን አጀህ/በርቱ በማለት ለመደለልና ለማዘናጋት በመጣር ላይ ነው። በኢትዮጵያ ፖለቲካ የሀገር ማዳን ትግሉን በተመለከተ ግን ይህ የወያኔን የግንቦት ምርጫ ጀሮም ቦታም ሊሰጠው የማይገባና ሕዝብም በዚህ ቀልድ ራሱን ሊጎዳ ከቶም እንዳይቀበል -- በምርጫ ተብዬው ላይ ማፅቀብ እንዲያደርግ -- የሚጠበቅ ነው።

ይልቁንስ ሕዝብ ሀገሩን ለማዳን ምን ማድረግ አለበት ለሚለው ተገቢውንና ተጨባጭ ተገባራዊ ምላሽ መስጠቱ ላይ ማተኮር ይኖርበታል። ይህንን በተመለከተም ለህብረተሰቡ ጥሪና የአዋጅ ከበሮም መመታቱ የሚታወስ ነው። ሀገራችንን ለማዳን ስንል ከማን የሚለው ጥያቄ ያው በራሱ ምላሽን ያገኘ ነው። ከወያኔ አረመኔ ቡድን የሚልም ነው። ይህ አረመኔና ፀረ ኢትዮጵያ ቡድን እድሜው ከተራዘመ ሀገሪቷን ይበልጥ ሊያደቅና ሊጎዳ እድል እንደሚያገኝም የሚታወቅ ነው። ስለዚህም የሕዝብና የሀገር ጠላት የወያኔ አገዛዝ፡ የነ መለስና ስብሃት ነጋ ቡድን መሆኑ ላይ ምንም ብዥታ ሊስተናገድ አይችልም። ሀገራችንን ለማዳን የወያኔ አገዛዝን ማቸነፍና ማስወገድ ይኖርብናል። ይህንን የዜጋ ተልዕኮ እንዴት ልንወታው እንሽላለን? በኢትዮጵያ ፖለቲካ የሥልጣን ማዕከል ፓርላማ ተብዬው የሆዳሞች መጠራቀሚያ አለመሆኑን በተመክሮ ያየነው ያወቅነው ነው። ሥልጣን ያለው በነመለስ ቡድን እጅ፡ የአፈናውን ተቋም በሚቆጣጠሩት የወያኔ ከፍተኛ ባለሥልጣናት እጅ ነው። ሥልጣንን ከነዚህ ፈልቅቆ ወስዶ ለሕዝብ ለማድረግ ወያኔዎች ራሳቸው የሚወዱትን ቃል እንጠቀምና እነ መለስ ዜናዊን ማምከንና ከጥቅም ውጪ ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ የሕዝብ መደራጀትና ለትግል መነሳት ወሳኝና አስፈላጊም ነው።

ድርጅት ወይም መደራጀት የሚያስፈልገው የተደራጀን ኃይል ማለትም ወያኔን ሳንደራጅ ልንጋተረውና ልናሸንፈው ስለማንችል ነው። ድርጅት ስንልም በተግባር ለሕዝብ የቆመውን፡ ፀረ ወያኔ አቋም ያለውንና ሕዝብን ሊያታግልም የተነሳውን እንጂ ተለጣፊውን ወይም በአገዛዙና ምርጫ በሚለው ሊያጅብ የተሰለፈውን አይደለም። ሕዝብ የሚበጀውንና አታጋይ ድርጅቱን ከአስመሳዩ መለየት መቻል አለበት። አለበለዚያ በአስመሳዮች ሊወናበድና ትግሉም ሊጎዳ ይችላል። ሀገር የማዳኑ ትግል መደራጀትንና የትግሉ ነው ሕይወቱ፡ ሀገሬን ማዳን ግዴታዬ ነው ብሎ መነሳትን ሲጠይቅ ግልፅ መሆን ያለበት ጉዳይ ሀገር ማዳን ግዳጅ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግማደ መስቀል መሆኑን ነው። ማንም ሌላ ሰው የሚሸከመው ግዳጅ አይደለም። ባዕዳን መጥተው ነፃ ያወጡናል ብሎ መጠበቅ ወይም መለማመኑ መጨረሻው የወያኔን ቀንበር ተሸክሞ መሰቃየት ነው። ሕዝብ የራሱንና የሀገሩን ዕጣ ፈንታ ወሳኝ ነውና ይህንን በመገንዘብ ለመራራ ትግል ራሱን ማዘጋጀት አለበት። የፋሺስት ኢጣሊያ ወራሪ ጦር በወቅቱ የነበሩትን ዘመናዊ መሳሪያዎችንና የመርዝ ጢሱንም ይዞ ሲመጣ አርበኞች ለሀገራቸው ሲሉ ደፍረው ተነስተው ገጠሙትና አሸነፉት እንጂ በዝምታ ቅኝ አገዛዙን አልተቀበሉትም። በሀገራችንም ለውጥ የመጣው በትግልና በመስዋዕትነት ነው።

ምንም እንኳ ሕዝብ የጠበቀውና የፈለገው ለውጥ ባይመጣም ሕዝባዊ ትግል ለውጦችን አዋልዷል። በብዙ ቦታ ለታሊያን ያደሩ ባንዶች ቢርመሰመሱም፣ ከዚያም ለአረመኔው መንግሥቱ ያደሩ ካድሬዎችና ሆዳሞች ቢበዙም ሁሉም ፋሺስት በየጊዜው ሸንፈትን ተከናንቧል። ይህ ቋሚ ሕግ ነው። ሕዝብ አምርሮ ከታገለ ማንናውም አምባገነን ይንኮታኮታል። የነመለስና ስብሀት ነጋም መጨረሻ ከዚህ የተለየ አይሆንም። የሕዝብ ቆራጥ ትግል አለሁ ብሎ ሲቀጣጠልና ሲነድ እሳቱ ለወያኔ ያደሩትን ሁሉ መለብለቡ አይቀርምና ከመለስ ጋር አይደለንም ብሎ ከዛሬው ማሳወቅ፣ ከወዲሁ መለየትና የሕዝብን ጎራ መጠጋት ወይም መቀላቀል የግድ ይሆናል።

ቅድሚያ ለተደራጀ ትግል መሆኑ እንዳለ ሆኖ ሀገርን ለማዳን ሕዝብ በየፊናው ሊወስዳቸው የሚችሉ ፀረ ወያኔ እርምጃዎች አሉ። እዚህ ላይ ዜጎች በቸልተኝነት ወይም በንዴት ራሳቸውን ባልሆነ መንገድ ለአደጋ ማጋለጥ የለባቸውም። ጥንቃቄና ኃይልን ቁጠባ ከትግል ማፋፋም ጋር ተቃራኒም አይደለም። ዜጎች በተቻለ መጠን ክፍፍልን መቋቋምና የኢትዮጵያዊነት ስሜትን ማጠናከር ይጠበቅባቸዋል። ኢትዮጵያዊ አይደላችሁም፣ የኢትዮጵያ ትግል አይመለከታችሁም እያሉ የሚሰብኩ ጠባቦች ወደዱም ጠሉም የወያኔ አጋር ናቸው። የሕዝብን የተባበረ ክንድ ያዳክማሉና። ክፍፍልን ያራግባሉና። ዜጎች በቡድንም በተናጠልም ፀረ ወያኔ ትግልን ማፋፋም ይችላሉ ብቻ ሳይሆን ማፋፋም አለባቸው። የሕዝባዊ አመጽ ትግል አንዱ አካል ዜጎች በየፊናቸው የሚያካሂዱት ትግል ነው። የሥራ ማቆም አድማ፣ የሙት ከተማ አድማ፣ ሰላማዊ ሰልፍ፣ ወዘተ የጋራ እንቅስቃሴን ጠያቂ ናቸው። ከዚህ ተያይዞ ደግሞ በውሱን ቡድንና በግለሰብ ደረጃ፣ በጎበዝ አለቃና በቀበሌም ደረጃ የሚተማመኑና የሚተዋወቁ ዜጎች በሶስትም በአምስትም ሰብሰብ ብለው እርምጃ መውሰድ ይችላሉ። ምን አይነት እርምጃ የሚለውም በተመክሯችን የታየ ቢሆንም በዚህም መጥቀስ ይቻላል። በሱዳን የተያዘውን መሬት በተመለከተ ዜጎች ታጥቀው መውሰድ የጀመሩት እርምጃ በራሱ አንድ ምሳሌ ነው። በገጠር ለምሳሌ የወያኔ እርሻዎች ማጥቃት፣ ሰብሉን ጎተራውን ማቃጠል ይቻላል። የወያኔ መኪናዎች ዕቃ የሚያጓጉዙበትን መንገድ መዝጋት፣ መኪናዎቹን ማበላሸትም ትክክለኛ የጥቃት እርምጃ ነው። በወያኔ ቅጥረኞች ላይ ከማግለል ጀምሮ ሌሎች ጠንካራ እርምጃዎችንም መውሰድ ያስፈልጋል።

በከተሞችም ተመሳሳይ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይችላሉ። የወያኔን እንቅስቃሴ የሚያደናቅፉ ሻጥሮች ሁሉ ትክክለኛና የሚደገፉ እርምጃዎች ናቸው። ዝርዝሩን ሕዝብ ራሱ ሊያውቀው የሚችል ነው። የአፋኝ ኃይሎችን መጓጓዣ ማበላሸት፣ የወያኔ ፋብሪካዎች እንዳያመርቱ ማደናቀፍ፣ ወዘተ አስፈላጊ ነው። በአፋኞቹ ላይም የሚያሸብርና የሚቀጣ እርምጃዎችን መውሰድ ይገባል። ማዕቀብም ፍቱን አቋም ነው። አድማዎችን ማደራጀትም አስፈላጊ ሆኖ ይገኛል። የወያኔ ተለጣፊዎችና ቅጥረኞችንም ማዋከብና የሕዝብ ቁጣ ሰለባ ማድረግ ለትግሉ ጠቀሜታ አለው። የወያኔ ሰላዮችንም በተቻለው መንገድ ሁሉ ማጋለጥና ሕዝብም ፊት እንዲነሳቸውና ተገቢውንም እርምጃ እንዲወስድ ማድረጉ ይጠቅማል። ሕዝብን ንቀውና ሆዳቸውንም አስቀድመው ከወያኔ ጎን የሚቆሙትንም ማጋለጥ ተገቢ ነው። ከባዕድ ሀገሮች እየተመለሱ የወያኔ አገልጋይና አውደልዳይ የሚሆኑትንም ማስደንገጥና አቋማቸውንም እንዲቀይሩ ማድረግም የሚቻል ነው። ሁለገብ ትግል ስንል ሁለገብ ግብግብና ጠርነት ነውና ሁሉም ዜጋ በትንሹም

በትልቁም፣ በፋብሪካውም፣ በትምህርት ቤቱም፣ በገጠርም በከተማም፣ በቀበሌም በከፍተኛም፣ በአየር መነገድም በወታደሩ ጦር ሰፈሮችም በፀረ ወያኔው እንቅስቃሴና ጥቃት በአቅሙ መሳተፍ ይችላል፣ አለበትም።

ቀደም ብለን እንደጠቆምነው መደራጀት ወሳኝ ነው። ተደራጅተው ሕዝብን ሊያታግሉ ከሚጥረው ኢሕአፓ ጋር መያያዝም፣ አብሮ መደራጀትም ያስፈልጋል። ወያኔ በዕብሪት ተወጥሮ የሕዝብን ወኔ ሰልቤያለሁ በሚል እምነትና የሚደፍረኝም የልም በሚል ተዝናንቶ ሊቀጥል ተነስቷልና ሕዝብ ይህ ሀሰት መሆኑን በተግባር ሊያሳየው ይገባል። ፍርሃትን ማሸነፍ ይቻላል። ክፍፍልንም ማስወገድ ይቻላል። ዋናው ቆርጦ መነሳትና ሀገርን ለማዳን መወሰን ነው። በዚህም መሰረት በተለይ ወጣቱን፣ ሴቶችን ማደራጀት ያስፈልጋል። ወጣቱ ክፍል ከተንቀሳቀሰ --ግዴታውንም አውቆ መንቀሳቀስ አለበት-- የወያኔ ተንኮል ይፈርሳል። የሀገራችን ወጣት ለሀገሩ እንዳይዋደቅ ወያኔ የተበተበው ሴራ ሁሉ ኢሚንት ይሆናል። ስለዚህም ወጣቱ ለሀገሩ እንዲቆም መቀስቀስ ዋና ተግባር ሆኖ ከፊታችን ይደቀናል ማለት ነው። ወጣቱ ከተደራጀና ወይም ሊታገል ከቆረጠ በድፍረትና በአፍላቂነት በወያኔ ላይ በቡድንም በተናጠልም ጀብድ ሊፈጽም የሚችል ነውና በዚህ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ወሳኝ ነው። ጨላማው የሚወገደው በዚህ አይነት መስዋዕትነት ጠያቂ ትግል ብዙዎች ሲሳተፉና ግራ ቀኙ፣ ገጠር ከተማው ለወያኔና ቅጥረኞቹ የቀውጢ ማዕከል ሲሆን ነው። ለሕዝብ ሰላም ከሌለ ለወያኔና ቅጥረኞቹም ምንም ሰላም ሊኖራቸው አይገባም። ትግላችን ይፋፋም።

„መልካም አስተዳደር ይዘቱን የሚገልፁ በርካታ ነጥቦች ቢኖሩም በዋናነት፣

1. የሕዝብ ተሳትፎ
2. የሕግ የበላይነት
3. ግልጽነትና ተጠያቂነት
4. ተግባራዊ ምላሽ ሰጪነት
5. የመግባባት ፖለቲካ አራማጅ
6. ትክክለኛነትና አጠቃላይነት
7. ቀልጣፋነትና ውጤታማነት የተሰኙት ይጠቀሳሉ።

የማንኛውም ሕብረተሰብ ደህንነቱና የሕይወት እስትንፋስ ያለው መሆኑ የሚረጋገተው ሁሉም አባላቱ የዚሁ ሕብረተሰብ አባል የመሆን ስሜት ሲኖራቸውና ያልተገለሉ መሆናቸው ሲረጋገጥላቸው ብቻ ነው። ይህ ሊረጋገጥ የሚችለው ደግሞ ሁሉም የሕብረተሰቡ አባላት በተለይም ደግሞ ለጥቃትና ለጉዳት የተጋለጡ ክፍሎች ሰብ አዊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሁም የነሳነት መብታቸው ያለምንም ገደብ ተከብሮላቸው የኑሮ ሁኔታዎቻቸውን ለማሻሻል እድሉ ሲኖራቸውና ይህንንም ለመጠቀም ሲመቻችላቸው ብቻ ነው። ይህ ባልሆነበት ሰላምና ማህበራዊ መረጋጋት፣ አንድነትና መተሳሰብ ይጠፋና ሕዝብም እንደ ሕዝብ፣ ሀገርም እንደ ሀገር የመኖር ዋስትና ሊኖራቸው አይችልም።“ ፍኖተ ዴሞክራሲ 2008 ዓ.ም.

## *ከኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ(ኢፖእአኮ) የተገኙ*

*„ለሰብአዊ መብት መታገል የሁሉም ዜጋ ግዴታ ነው። ለሰብአዊ መብት ሲታገሉ የወደቁትን መዘከር፣ ለእስር የተዳረጉትን መታደግ፣ የ እስረኛ ቤተሰቦችን ማገዝ፣ ተይዘው ደብዛቸው የጠፋውን እስረኞች ማስታወስ፣ ለአንድ ወይም ሁለት እስረኛ ሳይሆን ለሁሉም የፖለቲካ እስረኞች መጮህ ያስፈልጋል። ሰብአዊ መብት ተሸራርፎ የሚታይ አይደለም። ለአንዱ መብት ተከብሮ ለሌላው ሊሻር አይገባም፣ ተቀባይነትም አይኖረውም። ስለዚህም ፍትህ በተጓደለበት ሁሉ መቃወምና ለሁሉም ዜጋ ሙሉ መብት መከበር መቆም የግድ ነው። የሁልጊዜም ትግል ነው። በቃሊቲ፣ ላሉት ከጮህን በዝዋይ ዴዴሳ፣ አርባ ምንጭ፣ ጅጅጋ፣ ወዘተ ላሉትም የፖለቲካ እስረኞች ድምፃችን መሰማት አለበት። ከፖለቲካ አቋም መመሳሰል መለየት ባሻገር ፍትህ አልባ ለሚፈፀመው በደል ሁሉ ተቃዋሚ ሆነን መገኘት አለብን ማለት ነው። የኔ እስረኛ የእኛ እስረኛ የምንለው ሳይሆን የሁላችንም እስረኛ ብለን በጋራ መቃወምና ይፈቱ ጥሪን ማስተጋባት ይኖርብናል። ብርቱካን ሚደቅሳ፣ አበራሽ በርታና በየማጎሪያው ያሉት ሁሉ ሴት እስረኞች በአስቸኳይ ይፈቱ ማለት አለብን። ለአንድ ድርጅት አባል እስረኞች ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ድርጅቶች አባል እስረኞች ጩኸታችንን መስተጋባት ይኖርበታል።“*

**ለሰብአዊ መብት መታገል የዜግነት ግዳጅ ነው።**
ጥር 7/2002 ዓ.ም.

*„በዘልማድ ሰቶችን የመደብደብ ድርጊት በሀገራችን በሰፊው ሲፈፀም የቆየ ሲሆን ዛሬም በሰፊው መቀጠሉን የምናውቀው ነው። ሴትና ..... ካልተደበደበ ..... ወዘተ የሚሉ ኋላቀር አባባሎች ዛሬም አልተረሱም። የማይወራና የሚድበሰበስ ጉዳይ ሆኖ እንጂ ብዙ ሚስቶች በባሎቻቸው ይደበደባሉ። ህፃናት ሴቶችም እንዲሁ የድብደባ ሰለባ ናቸው። ለዘመናዊ ባርነት ወደ ባዕድ ሀገሮች በተለይም ወደ መካከለኛ ምሥራቅ ሀገሮች የተላኩ ወጣት ሴቶችም ብዙ ድብደባና ሁለገብ በደል ይደርስባቸዋል። ሴቶችን የመድፈር ወንጀልም መቀነስ ሳይሆን እየበዛ ነው። ያለው ሥርአት የሞራል ድቀትና የሥነምግባርን ዝቅጠት በማስፋፋቱ ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱ ሴቶች በዘመድ ሳይቀር በብዛት እየተደፈሩ መሆናቸው በየጊዜው እየተዘገበ ነው። ለአቅመ ሔዋን ሳይደርሱ የተዳሩና ጤናቸውም ኑሯቸውም የተበላሸ ብዙ ሺ ለጋ ዜጎች የዚሁ አሰቃቂ በደል ሰለባ ናቸው።“*

**በሴቶች ላይ የሚደርሰው በደል ያብቃ**

ኅዳር፡ 17/2002 ዓ.ም.

የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

February 10/2010

## OPEN LETTER TO PRESIDENT JACOB ZUMA
## PROTECT ETHIOPIAN REFUGEES IN SOUTH AFRICA

**On Februarz 7, shops owned by Ethiopians and other foreign nationals were looted and the refugees attacked in a service delivery protest that, as happened in july 2009, turned violent and xenophobic. The attacks took place in Siyathemba and Balfour townships.**

**The consortium for Refugees and Migrants in South Africa (CoRMSA) has added ist voice against these attacks which continue because the perprators are not brought to justice. A task force of Ministers which visited the affected townships, much as Your Excellency has done in a surprise visit, has not come up with any effective and sustainable solution. The refugees are being used as convenient excuses by protesting people and this must be stopped as it is unjust on all grounds. In July 2009, many Ethiopians, like Zimbabweans though in a lesser number, were victims of violence and looting and were displaced too. Most Ethiopians fled to South Africa to flee persecution much as South Africans come to Ethiopia as refugees during the Aparthied rule. South Africa must respect the right of refugees and protect Ethiopians from xenophobic violnce.**

**Excellency, Ethiopia is presently suffering under a one ethnic base dictatorship that has emerged as one of the worst human rights violators in the continent. It is not by accident that many Ethiopians face dangers and even death to make their way to South Africa ti find refuge. Hence, their refugee rights and saftey should not be compromised.**

**SOCEPP thanks Your Excellency.**

INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE
SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE

የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

February 11/2010

## NORWAY—STOP MISTREATING ETHIOPIAN REFUGEES

**SOCEPP has learnt taht a number of Ethiopian asylum seekers are undergoing mistreatment and undue incarceration in isolated camps. This is worrying and totally unjust and SOCEPP once again calls on the authorities in Norway to redress the situation without any procrastination.**

**Here below is a copy of a letter received by SOCEPP which details the situation in the camps of Norway.**

**"Dear SOCEPP**

**We, Ethiopians living in Norway, need your urgent help in forwarding our problem to the concerned authorities in Norway. The situation is as follows.**

**We are asylum seeker in Norway. Some of us heve been frozen in this situation for three years and most of us have stayed here from six years to ten years: All of us are political refugees, but, our applications were rejected at differenet timeson grounds we consider flimsy and unfounded. Noe we are in waiting camps or deportation camps in two places, namely FRAGERLI and LIRE, near to the Norwegian capital Oslo. It is the rule of Norwegian immigration that the maximum stay in these places be from two weeks to three months depending on the refugee; situation. But some of us have been in the camps for more than two years.**

**The situation of the camps:**

1. **We are not allowed to meet or be visited by any humanitarian organization. The camps are controlled by the Norwegian police.**
2. **The camps are very isolated from the society and we are unable to have access to the telephone and othe means of communications.**
3. **Not enough food, medication and clothing.**
4. **Five or six people are crammed in a single small room and as a result many refigees have fallen ill or have become depressed.**
5. **The situation has led to short tempers and frustration and often to fights. The police intervene and throw out the persons involved outside on the open ground.**

**Nobody seems responsible for these inhuman and degrading treatments of refugees in Norway. Many refugees have mental problems now and are permanently ill and have become usless even if they go back to their homeland. All the Ethiopians in these two camps are political refugees and they face deportation back to the repressive regime that has often disapeares or jailed refugees who have been deported. The mistreatment of refugees is an unjust act and the act of deportation is also against the International Covenant on Civil and Political Rights(ICCPR). which protects the refugees from sending back to countries where they face a serious risk of persecution or torture. The Human Rights Committee has interpreted article 7 of the ICCPR to forbid a return of persons to places where they would be at risk of torture or cruel, inhuman, or degrading treatment or punishment.**

**SOCEPP, please we need the urgent help of your office and that of all concerned international humanitarian organizations."**

**Norway, please end this injustice which stains your human rights record.**

INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE

SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE

# AFRICOM: A RECOLONIZATION FORCE?

**Lemma Tedla**

**Liberia has formally expressed its willingness to serve as the base for the American controlled African Command force which is now stationed in Germany. The African Command was established in October 2007 and activated a year later. Until their transfer to the Africa Command (AFRICOM) all 53 nations on the continent except for those in the Horn of Africa (covered by the Central Command) and the island nations of Madagascar and the Seychelles in the Indian Ocean (handled by Pacific Command) were within the area of responsibility of the European Command (EUCOM), whose top commander is simultaneously the Supreme Allied Commander of the North Atlantic Treaty Organization (NATO).**

**AFRICOM, whether based in Germany or Liberia, augurs more direct military intervention by the US in Africa. Until recently, Washington did not engage in full scale military intervention in Africa (bombing Tripoli and Khartoum, but the Mogadishu debacle was itself another deterrent) and had contented itself with indirect action like organizing assassinations (Lumumba), backing colonial forces (Portugal), Apartheid (South Africa ), arming pro American rebels (FLNA and UNITA in Angola, TPLF and EPLF in Ethiopia, Renamo in Mozambique, supporting dictators like Siyad Barre and Mobutu in Zaire, staging coups (Ghana). On their part, the French intervened militarily to pro up dictators or to support rebels (Chad, Cote d'Ivoire, Central African Republic), while Britain went after the diamonds in Sierra Leone and ended up by controlling the country as a whole. The setting up of AFRICOM**

**highlights America's determination to take the upper hand over its rivals (China mainly and France in a second degree).**

**The intensification of America's military intervention in Africa began with the so called Pan Sahel Initiative (PSI) with the deployment of Special Forces to Mali, Mauritania, Niger ( against Tuareg rebels) and other places in Western Africa. The Pan Sahel Initiative was succeeded by the Trans-Saharan Counterterrorism Initiative (TSCTI) in June 2005 which has American military personnel (1000 in number) assigned to eleven African nations: Algeria, Burkina Faso, Libya, Morocco, Tunisia, Chad, Mali, Mauritania, Niger, Nigeria and Senegal. The urgency for an AFRICOM was explained by AFRICOM commander General Ward in March 2008 as a result of "America's dependence on African oil" and the need "to combat terrorism". It is to be noted that prior to the formal launch of AFRICOM, the Pentagon conducted in 2008 the Africa Endeavour in which 23-nation military forces from Benin, Botswana, Burkina Faso, Burundi, Cameroon, Cape Verde, Chad, Gabon, The Gambia, Ghana, Kenya, Lesotho, Malawi, Mali, Namibia, Nigeria, Rwanda, Senegal, Sierra Leone, Uganda and Zambia took part. Since then, the US has trained African rapid intervention and counter insurgency forces and has used these for interventions (Ethiopia in Somalia and Darfur, Rwanda in the Congo and the Sudan, Uganda in the Congo and Somalia, etc). Washington does make the appropriate noises about human rights, development and general security concerns but the bottom line is that its main concern is the vast potential and riches of Africa. In its official web site, AFRICOM justifies its existence in the following terms:**

**"Africa is growing in military, strategic and economic importance in global affairs. However, many nations on the African continent continue to rely on**

the international community for assistance with security concerns. From the U.S. perspective, it makes strategic sense to help build the capability for African partners, and organizations such as the Africa Standby Force, to take the lead in establishing a secure environment. This security will, in turn, set the groundwork for increased political stability and economic growth".

However, Pentagon's contingent scenarios for the invasion of Nigeria and for naval control of Africa's off shore oil reserves and routes suggest different.

AFRICOM is arguably an American re colonization force enabling Washington to intervene at will and where need be to secure its strategic interests. The counter insurgency troops trained by the US from West Africa to the Horn are not only to be used locally to stamp out rebellions but also to act locally and regionally against threats to American interest. China is deep in competition countering the American presence and drive to impose monopolistic control. China arms and trains the forces several countries with oil and strategic minerals in their soil. In all cases, the hue and cry against terrorism in Africa is but a shroud, a cover. AFRICOM's primary mission is to secure oil and strategic minerals and to assure American supremacy in this campaign. Evidently Africa's main problems suggest bad governance and economic malaise but America's focus is not on these priorities though it is apparent that repressive regimes or no State countries like Somalia are fertile grounds for terrorism and violence. AFRICOM is a Bush legacy that seems to have been inherited without question by Obama. Alas, it not a measure geared to finding a solution compatible with African interests but a military contingency measure based on an alliance with African tyrants and aimed exclusively at assuring American dominance of Africa.

„ሀገር፥ ሕዝብ፥ ነፃነት፥ ዴሞክራሲና ነፃ ምርጫ አንዱ ከሌላው ተነጣጥለው የሚታዩ ባለመሆናቸው“

ምርጫን የምናየው ከኢትዮጵያ ሀገራችን የዘለቄታና ስትራተጂያዊ ራዕይ እንዲሁም
ከሕዝባችን መሰረታዊና ዘላለማዊ ጥቅም አኳያ በመሆኑ፥
ስለብሔራዊ ምርጫ ሲታሰብ ነፃና ርቱዕ ምርጫ ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ስለሚመነጭ፥

- የተሟሉ ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር፥
- የምርጫው ሕግ ፥ ደንብና ስነሥርአት ሁሉም ወገን አክብሮ መገኘት፥
- የምርጫው አስፈፃሚ አካል ነፃና ገለልተኛ መሆኑን ማረጋገጥ፥
- የመገናኛ ብዙሃን በ እኩል የመጠቀምና ሁሉም ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ለምርጫ የሚያስፈልጋቸው የገነዘብ ወጪ በእኩል የማግኘት መብት መከበር፥
- ተወዳዳሪዎች ከቦታ ወደቦታ በነፃና ያላንዳች ተፅዕኖ የመንቀሳቀስ፥ ሕዝብን የመቀስቀስና የማደራጀት መብት መከበር፥
- የሀገር ውስጥም ሆኑ የአለም አቀፍ ድርጅቶች በገለልተኛነት ታዛቢ የሚሆኑበት ሁኔታ መፍጠር፥
- የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መፈታት
- ወሳኝ ነው።“


FIKARE
P.O.BOX 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A

ዋጋ - US $ 3.00 or 3.00 Euro